ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 170 የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፎቶ - በሃዱሽ አብርሃ

# ሸገር ከተማን በቴክኖሎጂ ሽግግርና በኢኮኖሚ

## እንቅስቃሴዋ አርአያ የምትሆን ከተማ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሸገር ከተማ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ አርአያ የምትሆን ከተማ ለማድረግ በልዩ ትኩረት እንደሚሠራ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ።

የቆዳ ስፋቱ 160 ሄክታር የሆነውና በ12 ክፍለ ከተሞች እና በ36 ወረዳዎች እንደ አዲስ የተዋቀረው ሸገር ከተማ በትናንትናው እለት በይፋ ተመሥርቷል።

አቶ ሽመልስ፣ ሸገር የሕዝቡን ባሕል በማበልጸግ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ መልካም ምሳሌ የምትሆን ከተማ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል።

በሸገር ከተማ ለከተማ ግብርና የተሰጠው ትኩረት የላቀ መሆኑን የገለጹት አቶ ሽመልስ፤ ከዚህ አንጻር በከተማ ግብርና የተሰማሩ ባለሀብቶችና አርሶ አደሮች በጋራ የሚሠሩበት ሁኔታ መመቻቸቱን አስታውቀዋል።

በአገሪቱ የትግል ታሪክ መሬት የአርሶ አደሩ እንዲሆን ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በአንጻሩ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች ከልማት ተገለለው ከቀያቸው ተፈናቅለው ፈርጀ ብዙ በደል ደርሶባቸዋል ብለዋል።

የከተማዋ መሬት ከሙስናና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ ሥራ ላይ ውሎ ለከተማዋ ነዋሪዎች ኑሮ መሻሻል ብሎም ለሀገር እድገት አስተዋፅኦ

ሸገር ከተማን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ሽመልስ አብዲሳ



## በግማሽ ዓመቱ ከማዕድን ዘርፉ የተገኘው ገቢ ዝቅተኛ ነው

- 324 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ታቅዶ 115 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል
- ሕገወጥ ግብይትና የጸጥታ ችግር ዘርፉን ፈትነውታል

ገጽ 4

# ባለፉት ሰባት ወራት ከቡና ወጪ ንግድ 702 ሚሊዮን ዶላር ተገኘ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት ከቡና ወጪ ንግድ ወደ ተለያዩ የዓለም መዳረሻ ሀገራት ከተላከ የቡና ምርት 702 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን የቡናና ሻይ ባለስልጣን ገለጸ።

በባለስልጣኑ የገበያ መረጃና ደህንነት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ቸሩ ኮሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሰባት ወራት 126 ሺ 649 ነጥብ 02 ቶን በመላክ 702 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን



ባለፉት ሰባት ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




















ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አቶ አወሉ አብዲ

## ክልሉ ድርቅን ለመቋቋም እቅዶችን ቀርፆ ወደ ሥራ ገብቷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በየዓመቱ ድርቅ የሚያስከትለውን አደጋ ለመቀነስ በኦሮሚያ ክልል የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅዶች ተቀርጸው እየተሠሩ መሆኑን የክልሉ መንግሥት አስታወቀ።

ሰላምን ለማረጋገጥ፣ ልማቶችን ለማስፋፋትና ድርቅን ለመቋቋም ጠንካራ ሥራዎች እየተሠሩ ስለመሆኑ በትናንትናው ዕለት የኦሮሚያ ክልል በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ተገልጿል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፣ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ጊዜያት ድርቅ የሚያስከትለውን አደጋ ለመቀነስ የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅዶች ተቀርጸው እየተሠሩ ነው። በአጭር ጊዜ እቅድ ለዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እየተደረገ ነው። በተለይ ውሃ፣ የሕክምና ቁሳቁስ እንዲሁም አልባሳት እንዲደርሱ ተደርጓል። ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዳይስተጓጎሉ የምገባ ፕሮግራም በስፋት እየተተገበረ ነው። በተከናወኑ ቅንጅታዊ ተግባራት እስከአሁን በዜጎቻችን የሕይወት ማለፍ አልደረሰም። ባለፈው ዓመት ከሦስት ሚሊዮን ኩንታልና ከ10 ቢሊዮን ብር በላይ ለ7 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዜጎች እርዳታ በመስጠት የአንድም ዜጋ ሕይወት እንዳያልፍ ተደርጓል። በዚህም ዓመት የተረጂዎች ቁጥር ወደ አራት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዝቅ ማለቱንም አንስተዋል።

እንደ አቶ አወሉ ገለጻ፣ ድርቅ በየዓመቱ የሚከሰት በመሆኑ ከረጅም ጊዜ አንጻር ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም በየዓመቱ ከአራት እስከ አምስት ቢሊዮን የተለያዩ ችግኞችን በመትከል የአየር ሁኔታው ከሞላ ጎደል ወደ ነበረበት እንዲመለስ እየተደረገ ነው። የጠፉ የውሃ ምንጮች ዳግም እየመጡ ነው።

በጦርነትና በድርቅ ወቅት ችግር የሚደርስባቸው ሕፃናትና ሴቶች በመሆናቸው የተመጣጠነ ምግብ ከማግኘት አንጻር የ«ሌማት ትሩፋት» ፕሮግራም ተነድፎ እየተሠራ ነው። ድርቅ በየዓመቱ የሚከሰት ችግር በመሆኑ «ቡሳ ጎኖፋ» በሚል፣ ሰው ለሰው የሚደርስበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል ያሉት አቶ አወሉ በዚህም ሀብት ተሰብስቦ ለሕዝቡ እንዲደርስ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

በተጨማሪም የተማሪዎች ምገባን በማጠናከር በድርቅ ምክንያት ትምህርት ቤቶች እንዳይዘጉ እየተሠራ ነው።

ድርቅን ለመቋቋም ከተቀረጹ የረጅም ጊዜ እቅዶች መካከል የውሃ ልማት ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ነው። በቦረና፣ በባሌ እና በሐረርጌ ዞኖች የውሃ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ መሆኑን አቶ አወሉ ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት ድርቅ በምስራቅ አፍሪካ የከፋ ችግር እያደረሰ መሆኑን ያነሱት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ በኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልል በአስር ዞኖች ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የዝናብ እጥረት በመኖሩ ድርቅ መከሰቱን አንስተዋል። ይሁን እንጂ በተሠራው ሥራ ዜጎች በምግብ ችግር እንዳይጎዱ ተደርጓል።

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ እንደገለጹት፣ በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች የተከሰቱ ችግሮችን ወደ ሰላም ለመመለስ በትኩረት ሲሰራ ቆይቷል። አሁንም እየተሠራ ነው።

የበጋ ስንዴ ልማት ላይ የተሠሩ ሥራዎች፣ በምግብ ራስን ከመቻል አልፎ የሀገርን ኢኮኖሚ እስከመደገፍ ተደርሷል። ድርቅ ሀገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለማቀፋዊ ችግር እየሆነ መምጣቱን አንስተው፣ በኢትዮጵያ በየአስር፣ በአምስትና በየዓመቱ እየተመላለሰ በሰውና በእንስሳት ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ገልጸዋል።

# በክልሉ ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከ100 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

**በሪሁ አረጋ**



አዲስ አበባ፡- በክልሉ ሁለት ሺህ 434 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መሸፈኑንና ከዚህም ከ100ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበከር ካሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በክልሉ በአጠቃላይ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከተሸፈነው ሁለት ሺህ 434 ሄክታር መሬት ከ100 ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል።

በበጋ መስኖ የለማው የስንዴ ሰብል የመሰብሰብ ደረጃ ላይ መድረሱን የገለፁት አቶ ባበክር፣የደረሰውን ሰብል ለመሰብሰብም ኮምባይነሮችን የማዘጋጀት ሥራ ተጠናቆ ከመጪው ሳምንት ጀምሮ የተጠናከረ የመሰብሰብ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ ለዳቦ ፋብሪካዎች በቂ የሆነ ስንዴ ምርት በማቅረብ የክልሉን የዳቦ ፍጆታ ለመሸፈን ያስችላል ሲሉ ኃላፊው ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ክልሉ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ልምድ እንዳልነበረው የጠቆሙት አቶ ባበከር፣ የተጀመረው ሥራ የክልሉን የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አልፎ ጎረቤት ሀገር ምርቱን በማቅረብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግ የሚቻል መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት ስንዴ አብቃይ ያልሆኑ የክልሉ አካባቢዎች ጭምር በበጋ መስኖ ስንዴ ወደ ማምረት እየመጡ መሆኑንም ገልጸዋል።

በክልሉ ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ብዙ ተሞክሮዎች እየተገኙበት ነው ያሉት ኃላፊው፣ የስንዴ ልማቱ ጥሩ በሆነበት አካባቢ ላይም በሄክታር እስከ 70 ኩንታል ድረስ ምርት የሚገኝበት ሁኔታም እንደሚኖር አመልክተዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ማኅበረሰቡ የተሻለ ልምድ እንዲኖረው በማድረግ መቼ መዝራት እንደሚገባ፣ ለሰብሉ ምን ምን ግብዓቶች እንደሚያስፈልጉት በመለየት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ተሠርተዋል ሲሉ የቢሮ ኃላፊው ገልጸዋል።

ለቀጣይ የክረምት ስንዴ ልማትም ወሳኝ ተሞክሮ የተቀሰመበትና መሬት በአግባቡ ተዘጋጅቶ ከተዘራ ለውጥ የሚያመጣ ምርት ማግኘት እንደሚቻል የተገነዘብንበት ነው ሲሉም ኃላፊው ተናግረዋል።

እንደ አቶ ባበከር ገለጻ ፤የክልሉ ማኅበረሰብና አመራሮች በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ላይ ያሳዩትን ርብርብ በቀጣይ ክረምት ወቅት መድገም አለባቸው።

# በአፋር ክልል ከ139 ሺህ በላይ የ7ኛና 8ኛ ክፍል መጽሐፍት ተሰራጨ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል ከ139 ሺህ በላይ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍት ማሰራጨቱን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅትና መማር ማስተማር ዳይሬክተር አቶ ዋልዶ ሀይሰማ እንደተናገሩት፣ ክልሉ ያሳተመውን 139 ሺህ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍትን አሰራጭቷል።

የአዲሱ ካሪኩለም የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ታትመው ሲደርሱ በተለያዩ የማጓጓዣ አማራጮች እንዲሰራጩ ተደርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

ቀሪዎቹ መጽሐፍት በቀጣይ ወራት ሕትመታቸው አልቆ ወደ ትምህርት ቤቶች እንደሚደርሱ ይጠበቃል ያሉት አቶ ዋልዶ፣ በአጠቃላይ የተማሪዎቹ መማሪያ መጽሐፍት በአንድ ወር ውስጥ ታትመው ይደርሳሉ። በቀጣይ የማሰራጨት ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

የ2015 በጀት ዓመት አዲሱ የትምህርት ካሪኩለም ሙከራ የተደረገባቸው ሞዴል ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ መደረጉን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፣ በተቀሩት ትምህርት ቤቶች ላይ ደግሞ በሶፍት ኮፒ መጽሐፍቱ እንዲደርሳቸው መደረጉን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ የመምህራን መምሪያ መጽሐፍት በመታተሙ በቀጣይ ሙሉ በሙሉ ተደራሽ የሚሆንበት ዕድል አለ። የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት ደግሞ ሕትመቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በመምህራን ላይ ጫና ቢኖረውም ችግሩን የመምህራን ማስተማሪያ መድረሱ ችግሩን ሊያስታገሰው ይችላል ብለዋል።

የመጽሐፍት ተደራሽነት ችግር እንደሀገር ያለ ችግር ነው፤ የማተሚያ ቤቶች ግብዓት እጥረት ሕትመት ማጓተት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመኖሩ በሰዓቱ ለማድረስ ችግሩ ገጥሟል ሲሉ ተናግረዋል።

የሕትመት ሥራ በጥራትና በፍጥነት ሊያከናወን የሚችል ድርጅት እንደሀገር ባለመኖሩ የካሪኩለም ዝግጅቱ ተጠናቅቆ በወቅቱ ማቅረብ አለመቻሉን ጠቁመዋል።

ቀደም ሲል በፌደራል ደረጃ ይዘጋጅ የነበረውን አሠራር በመቀየር በአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍት በክልሉ መዘጋጀታቸው ለየት የሚያደርገው አሠራር ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀው ካሪኩለም መልባ በተሰኘው ማተሚያ ድርጅት ጋር ውል ተገብቶ እየታተመ ይገኛል ብለዋል።

ዜና

# ኢትዮጵያ ውስጥ ከተሠሩ ጆርናሎች ውስጥ በዓለምአቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙት አራት ብቻ ናቸው

## - በምርምር ዘርፍ ዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ መስፈርትን ያሟሉ ዩኒቨርሲቲዎች በሀገር ደረጃ የሉም

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በተመራማሪ፣ በሀብት ብዛትና በዩኒቨርሲቲ ቁጥር የተሻለች ሀገር ብትሆንም ዩኒቨርሲቲዎቿ በምርምር ዘርፉ የዓለማቀፍ መስፈርትን ያሚሉ አይደሉም። በተመሳሳይ በዓለምአቀፍ ደረጃ እውቅና ያስገኙት ጆርናሎች ብዛት እስከ 2022 ድረስ አራት ብቻ መሆናቸውን በትምህርት ሚኒስቴር የምርምር ጉዳዮችና የማኅበረሰብ ጉድኝት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን ቢኖር ገለጹ።

ዶክተር ሰለሞን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ እንደሀገር በዓመት ብቻ ሳይሆን በወራትም ጭምር የሚታተሙ አዳዲስ ጆርናሎች አሉ። በዚህም እስካሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ከ185 እስከ 200 የሚደርሱ ጆርናሎች ታትመዋል። ሆኖም በዓለማቀፍ ደረጃ ያለው ቅቡልነት ዝቅተኛ ነው። እስከ 2022 ድረስ ባለው መረጃ አራት ጆርናሎች ብቻ ናቸው ዓለም እውቅና የሰጣቸው።

ኢትዮጵያ ባላት የከፍተኛ ተቋማት ብዛት ፤ በሕዝብ ቁጥር ከደቡብ አፍሪካ ትበልጣለች። ሆኖም ደቡብ አፍሪካ እስከ 2022 ድረስ ባለው መረጃ ከ125 በላይ የሆኑ ጆርናሎች ዓለማቀፋዊ እውቅናን አግኝታለች። የሳይንቲፊክ መስፈርቱን አሟልተውም ሀገርን በመወከል ሌሎች እንዲጠቀሙባቸው ማድረግ መቻላቸውን የጠቆሙት ዶክተር ሰለሞን፤ ለዚህ ያበቃቸው ብሔራዊ ተቋም ተመሥርቶላቸው መንግሥት ከሚበጀተው በጀት



ዶክተር ሰለሞን ቢኖር

በላይ የራሳቸው ገቢ በምርምር እንዲያመነጩ መደረጉ ነው። እንደእኛ ሀገር ግን ይህ የለም። ስለዚህም መታሰብ ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

አንድ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ቢያንስ የሰው ኃብቱን፣ የግብዓት አቅርቦቱን ማሟላት ሲችልና ጆርናሎችን የማሳተም ብቃት ሲኖረው ነው ያሉት ዶክተር ሰለሞን ዩኒቨርሲቲዎች ግን ይህንን ማሟላት አይችሉም ብለዋል።

እንደ መንግሥት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወደ መስመሩ እንዲገቡ የማስቻል ሥራ ተሠርቷል የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ተብለው የተለዩት ነባር የተባሉት ሲሆኑ፤ እነርሱም አዲስ አበባ፣ ሐዋሳ ፣ ጅማ ፣ መቐሌ ፣ ጎንደር ፣ ባህርዳር ፣ ሐረማያ እና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሰለሞን ገለጻ፤ ከዚህ በኋላ በሚኖራቸው ጉዞ ቢያንስ አንድ ጆርናል ሊያሟላው የሚችለውን አነስተኛ ዓለምአቀፍ ሳይንሳዊ መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል። የቀጣይ የኢትዮጵያን ዓለማቀፍ የምርምር እውቅናን የሚያሻሽሉት እነርሱ በመሆናቸው ተቋማቱ በምርምርና ጥናታቸው የተሻሉ እንዲሆኑም ልዩ ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

እስካሁንም ለ39 የሚደርሱ ጆርናሎች እውቅና እንደተሰጠ የጠቆሙት ዶክተር ሰለሞን፤ በሀገር ደረጃ ዓለማቀፋዊ የሳይንስ መስፈርትን ይዞ የተመዘነ ነው። ይህ ደግሞ በአፍሪካ ብሎም በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሰፋላቸው እድል ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም የሀገር ገጽታን ከመገንባቱና ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች በዓለማቀፉ ደረጃ ሀገርን የሚያስጠራ ምርምር እንዲሠሩ ያግዛቸዋል ብለዋል።

የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው በሀገሪቱ በሚቋቋም የምርምር ጆርናሎች ድረ-ገጽ እና መረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገቡና ተደራሽ እንዲሆኑም ያስችላል። የጆርናሎችን ጥራት እና እይታም ይጨምራልም። በዓለም አቀፍ ምርምር መረጃ ሥርዓት (International Indexing Databases) ለመካተት በትጋት እንዲሠሩ ያስችላቸዋል ነው ያሉት ዶክተር ሰለሞን።

# አፍሪካ የሚካሄድባትን የመረጃ ጦርነት ለማሸነፍ ጠንካራ ሚዲያ ሊኖራት ይገባል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ የሚካሄድባትን የመረጃ ጦርነት ማሸነፍ የምትችለው ጠንካራ ሚዲያ ሲኖራት መሆኑን የዘርፉ ምሑራን ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት እና የሥነ-ተግባቦት ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የዓለም የፖለቲካ ሥርዓት በምዕራባውያን ሚዲያ የሚዘወር ነው። በመሆኑም አፍሪካ በምዕራባውያን ሚዲያዎች መዘወርንና የሚደረግባትን የሚዲያ ጦርነት ለመቋቋም የሚያስችል ጠንካራ የሚዲያ ተቋም ሊኖራት ይገባል።

ዓለም ላይ ከሚስተዋለው የመረጃ ጦርነት አሸናፊ ለመሆን ጠንካራ ሚዲያ አፍሪካ ሊኖራት ይገባል ያሉት ዶክተር ሳምሶን፤ ይህንን አፍሪካውያን ማሳካት ከቻሉ የመረጃ ጦርነቱ ላይ ቢያንስ አቻ መሆን የሚያስችላቸውን አቅም ያገኛሉ ብለዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን ገለፃ፤ አሁን እንደ ቀድሞው ጊዜ መሣሪያ ይዞ ሀገራት ላይ ጫና መፍጠር አይቻልም። ጦርነቱ የመረጃ፣ የሥነ-ተግባቦት እና የቴክኖሎጂ ነው። በሀገራት ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚሞከረው በዚሁ መንገድ እንደሆነ ሁሉ በአፍሪካ አህጉር ላይም ተመሳሳይ ተጽዕኖዎች ይታያሉ። ይህንን ለመከላከልም አፍሪካ የራሷን ጠንካራ የሚዲያ ተቋም ማቋቋም ይኖርባታል።



የምዕራባውያን ተጽዕኖ አፍሪካ ላይ በሰፊው ይስተዋላል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን፤ ምዕራባውያን የሚፈልጓቸውን አመለካከቶች አፍሪካ ላይ ለመጫንና የአፍሪካ ኢኮኖሚ በራሳቸው እንዲዘወር የሚያደርጉበት መሣሪያ ሚዲያ ሆኗል ብለዋል።

በመሆኑም አፍሪካ የራሷን ጠንካራ ሚዲያ በመፍጠር አንድ የሆነች አፍሪካን መገንባት እና ገጽታዋን የመቀየር ሥራ መሥራት ይኖርባታል ነው ያሉት። አፍሪካ ሊኖራት የሚገባው ሚዲያ እጅግ ከፍተኛ የሙያ ፍቅር እና ዕውቀት ያላቸው ጋዜጠኞችን የያዘና በፋይናንስ አቅሙም የተደራጀ መሆን አለበት ሲሉም አስተያየታቸውን አክለዋል።

የአፍሪካ መንግሥታት በበኩላቸው በሚችሉት ሁሉ በመተጋገዝ አፍሪካን የሚመስል ሚዲያ ማቋቋም ላይ መትጋት አለባቸው ብለዋል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት እና የስነተግባቦት መምህር ደናሰው ሽመልስ በበኩላቸው፤ የምዕራባውያን ሚዲያዎች በአመዛኙ አፍሪካ የጨለማ አህጉር እንደሆነች ለመሳል እና እራሳቸውን ደግሞ ከጨለማ አውጪ አድርገው ይስላሉ ሲሉ ተናግረዋል።

አሁን ላይ አፍሪካ የራሷ የሆነ የሚዲያ ተቋም እንዲኖራት መታቀዱ የአፍሪካን ገጽታ ሊያበላሹ ከሚችሉ የሌሎች ምዕራባውያን የሚዲያ ተቋማትን ተጽዕኖ እንድትቋቋም ያስችላታል ነው ያሉት።

አፍሪካ ሚዲያ ማቋቋሟ በትክክል አፍሪካ ስላላት ባሕል እና ማንነት ለሌሎች ዓለም ሃገራት ለማሳየት ይረዳል። በሚዲያ ከሚመጡ ተጽዕኖዎች አፍሪካ እራሷን እንድትከላከል ያደርጋልም ብለዋል።

ምዕራባውያን አፍሪካ ላይ የራሳቸውን ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የበላይነት አስጠብቀው ለመኖር በሚዲያዎቻቸው ስለአፍሪካ የተሳሳተ ወይም የተዛባ መረጃዎችን መስጠትን እንደ አንድ መንገድ ይጠቀማሉ ያሉት መምህሩ፤ አፍሪካ የራሷ የሆነ ሚዲያ ሲኖራት ትውልዱን የምዕራባውያን ተጽዕኖ እንዲቋቋም እንደሚያስችለው አብራርተዋል።



አቶ ፍሬዘር አያሌው

# ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች 4 ደርሰዋል

## - 9 የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎቱን በ1 መስኮት እየሰጡ ይገኛል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ቁጥር አራት መድረሱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ። ዘጠኝ የፋይናንስ ተቋማት ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎቶችን በአንድ መስኮት እየሰጡ መሆኑ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ሱፐርቪዥን ዳይሬክተር አቶ ፍሬዘር አያሌው በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አራት ባንኮች ሙሉ በሙሉ የሸሪዓ ሕግጋትን በተከተለ መንገድ ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ናቸው።

አቶ ፍሬዘር እንዳስታወቁት፤ ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ባንኮች ዘርፉ ላይ የተለያዩ ዝግጅት የሚያደርጉ አክሲዮን ማኅበራት በመኖራቸው በቀጣይም ወደ ሥራ የሚገቡ እንዳሉ ይጠበቃል።

ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ የፋይናስን አገልግሎት ከሚሰጡት ባንኮች በተጨማሪ ዘጠኝ የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎቱን በአንድ መስኮት እየሰጡ መሆኑን ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

በንግድ ባንኮች እየተሰጠ የሚገኘው የአንድ መስኮት ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ከመደበኛው የባንክ አገልግሎት በተጓዳኝነት የሚሰጥ መሆኑን አቶ ፍሬዘር ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የተለያዩ የግል ባንኮች የልዩ ፍላጎት ተቀማጭ ሒሳብ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎቱ በአማራጭነት እያቀረቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ ከወለድ ነፃ የኢንሹራንስ አገልግሎት ለማቋቋም የሚረዳ የሕግ ማዕቀፍ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ የሆነ አሠራር ያለው የኢንሹራንስ ኩባንያ ባይኖርም፤ በቀጣይ እራሱን የቻለ ከወለድ ነፃ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚያቀርብ ተቋም እንደሚፈጠር ይጠበቃል ብለዋል።

የኢንሹራንስ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈልጉ ደንበኞች የኢንሹራንስ ፈንድ ያቋቁሙና ጉዳት በሚያጋጥምበት ወቅት ባዋጡት ገንዘብ መሠረት ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሠራርን የያዘ መሆኑን አስረድተዋል።

ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሸሪዓ እስላማዊ ሕግ የፋይናንስ መርሆዎችን በተከተለ መንገድ የሚሠራበትና ምንም አይነት ወለድ (Interest) መክፈል ወይም መቀበልን የማይፈቅድ የባንክ አገልግሎት ሥርዓት ነው።

ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ባካተተ መልኩ አገልግሎታቸውን እንደሚሰጡ ይጠበቃል ያሉት አቶ ፍሬዘር፤ እንደማንኛውም አማራጭ የፋይናንስ አገልገሎቶች አቅራቢ ተቋም መታየት ይኖርባቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ ከኢስላሚክ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር መሐመድ አል ጃስር ጋር መገናኘታቸውንና በኢትዮጵያ ስላሉ የሥራ እንቅስቃሴዎች የተለያየ ድጋፍ በመፈለግ ዙሪያ መወያየታቸውን በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው ማስፈራቸው የሚታወስ ነው።

# ኮርፖሬሽኑ ከ 77 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ገበያ ሽያጭ አከናውኗል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ ፡- በግማሽ ዓመቱ ከ77 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ንግድ ሽያጭ ማከናወኑን የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታውቋል ።

የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳለው፤ ኮርፖሬሽኑ የወጭ ንግድ አፈጻጸምን ለማሳደግ ፤በሀገር ውስጥና በውጭ በተካሄዱ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ላይ አቅዶ በመሳተፍ ላይ ይገኛል። በዚህም በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ከስድስት ሺህ 500 ኩንታል በላይ የቡና፣ ፍራፍሬ፣የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ለውጭ ገበያ ሽያጭ አቅርቦ ከ77 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አግኝቷል ።

ለውጭ ገበያ የሚያቀርባቸውን ምርቶች በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራ መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ ኮርፖሬሽኑ በ2015 በጀት ዓመት የስንዴ ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ገልጿል ።

ስንዴ ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ኮርፖሬሽኑ ከዩኒየኖች ፣ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤ ከአምራቾችና ነጋዴዎች ምርትን በማሰባሰብ ስንዴውን አበጥሮ እና አዘጋጅቶ ለዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች እና ወደ ጎረቤት ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማግኘት እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሷል።

እንደ መግለጫው ከሆነ በኮርፖሬሽኑ ለገበያ የቀረበው ምርት ከ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ያደረገ ሲሆን ከእቅዱም በመጠን 111 በመቶ በዋጋ ደግሞ 98 በመቶ አፈጻጸም ማስመዝገቡን አብራርቷል።

ከተገኘው ጠቅላላ ሽያጭ ገቢ 93 ነጥብ 1 በመቶ ከሀገር ውስጥ ሽያጭ ገቢ የተገኘ ሲሆን ቀሪው 9 ነጥብ 6 በመቶ ከወጪ ንግድ የተገኘ መሆኑን በመግለጫው ጠቅሷል ።ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 41 በመቶ ብልጫ መኖሩን አመልክቷል።

በተያያዘም ኮርፖሬሽኑ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ገልጿል ።

በዚህም ለመንግሥት ሠራተኞች፣ለማረሚያ ቤቶችና ለኅብረተሰቡ፣ በቆሎ ፣ጤፍ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ስኳርና የፓልም ዘይት በተመጣጣኝ ዋጋ አቅርቧል።

ከዚህም በተጨማሪ በግንባታው ዘርፍ እየገጠሙ ያሉ ከፍተኛ የሆነ የሲሚንቶ እጥረት ለመቅረፍ ከፋብሪካዎች በቀጥታ በመረከብ ከ500 ሺ ኩንታል በላይ ሲሚንቶ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨቱን በመግለጫው ጠቅሷል። በመግለጫው ኮርፖሬሽኑ የሚያቀርብበት ዋጋ ከነፃ ገበያ ጋር ሲነፃፀር ከአንድ ነጥብ 6 እስከ 86 በመቶ የዋጋ ልዩነት መኖሩን ጠቁሟል።

# በግማሽ ዓመቱ ከማዕድን ዘርፉ የተገኘው ገቢ ዝቅተኛ ነው

## - 324 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ታቅዶ 115 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል

## - ሕገወጥ ግብይትና የጸጥታ ችግር ዘርፉን ፈትነውታል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ስድስት ወራት 115 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ። ሕገወጥ ግብይትና የፀጥታ ችግር የማዕድን ዘርፉ ዋነኛ ተግዳሮቶች መሆናቸው ተገልጿል።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ባለፉት ስድስት ወራት በማዕድን ዘርፉ 324 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ የተገኘው 115 ሚሊዮን ዶላር ነው።

የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ከዕቅዱ አንጻር 35 በመቶው ብቻ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን በዋናነት ሕገወጥ ግብይትና የፀጥታ ችግሮች ተግዳሮት መሆናቸውን አስረድተዋል።

በስድስት ወራት ውስጥ በማዕድን ዘርፍ ክፍለ ኢኮኖሚው 1 ሺህ 584 ነጥብ 14 ኪሎ ግራም ወርቅ ተገኝቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከዚህ ውስጥ 1ሺህ 121 ነጥብ 5 ኪሎ ግራም የወርቅ ምርቱ ከኩባንያዎች የማዕድን ቁፋሮ ሥራ የተገኘ ሲሆን፣ 462 ነጥብ 64 ኪሎ ግራም ወርቅ ደግሞ በባሕላዊ መንገድ መገኘቱን ገልፀዋል።

አቶ ሚሊዮን እንደገለፁት፤ በግማሽ ዓመቱ በተጨማሪም 76 ነጥብ 2 ቶን የታንታለም ምርት ተገኝቷል። በአጠቃላይ 41 ነጥብ 55 ቶን ለጌጣጌጥ ምርት የሚያገለግሉ ማዕድናት ተመርተዋል።

በማዕድን ዘርፉ ከተገኘው ምርት 3 ሺህ 330 ቶኑ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚያገለግሉ ማዕድናት መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል።



**አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ**

የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው ላይ የሚያለሙ ኢንቨስተሮች ለሚያለሙበት አካባቢ የሚከፍሉት "የሮያሊቲ" ክፍያ አለ፤ በስድስት ወራት ከሮያሊቲ ክፍያ 272 ሚሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል።

በተጨማሪ ከፈቃድ ማውጫ፣ ከመመዝገቢያ፣ ከማደሻና ከሙያ ብቃት ክፍያ 970 ሺህ ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትን ከማኅበረሰብ ትስስር ማጎልበት ጋር በተያያዘ ከማዕድንና ነዳጅ አልሚዎች 14 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ለአካባቢና ማኅበረሰብ ልማት ፈንድ መሰብሰብ ተችሏል።

በማዕድን ዘርፍ ሥራ በስድስት ወራት ውስጥ ከ89 ሺህ 800 በላይ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ ከዚህም ውስጥ 1ሺህ 405 የሥራ ዕድሎች በኩባንያዎች በኩል፤ 88 ሺህ 414ቱ ደግሞ በባህላዊ የማዕድን አምራች ኢንተርፕራይዞች በኩል የተፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ የማዕድን ልማትና ቁፋሮ የተካሄደባቸውን ቦታዎች ላይ የአካባቢ ጥበቃና መልሶ ማገገም ሥራ ከማከናወን አንጻር ሁለት ሄክታር መሬት ላይ መልሶ የማልማት ሥራ ተከናውኗል።

ማዕድናት በሚመረትባቸው አካባቢዎች የፀጥታ ችግሮች መኖር፤ የኩባንያዎችና የማዕድን አምራች ኢንዱስትሪዎች የአቅም ውስንነት፤ ሕጉ ከሚፈቅድላቸው የጊዜ ገደብ በላይ በእጃቸው ወርቅ ይዘው የሚቆዩ አቅራቢዎች መኖር ለዘርፉ ዕድገት ችግር መሆኑን አቶ ሚሊዮን አስረድተዋል።

ለማዕድን ኢንዱስትሪዎች የመለዋወጫና የግብዓት መግዣ የሚውል የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እጥረት፣ የከበሩ ማዕድናት ሕገ ወጥ ግብይት መስፋፋት ተጨማሪ ፈተናዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በተለይ ወርቅ በብዛት በሚመረትባቸው ክልሎች በየደረጃው ያሉ አመራሮች ሕገ-ወጥ የማዕድናት ምርትና ግብይትን በመከላከል በኩል ደካማ የክትትል ሂደት ማሳየታቸውን አቶ ሚሊዮን ተናግረዋል።

አቶ ሚሊዮን እንደገለጹት፤ የማዕድን ዘርፉን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ ከጸጥታ አካላት፣ ከጉምሩክና ከሚመለከታቸው ተቋማት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልል፣ በኦሮሚያና ጋምቤላ ክልሎች ግብረ-ኃይል አሰማርቶ ሰፊ የቁጥጥር ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

የተለያዩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ላይ የሚስተዋለውን የፀጥታ ችግር ለመፍታትና የማዕድን ገቢውን ለማሳደግ ከፀጥታ ተቋማትና ከየክልሉ አስተዳደሮች ጋር በቅርበት እየተሠራ ነው ብለዋል።

# ሸገር ከተማን በቴክኖሎጂ ሽግግርና በኢኮኖሚ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲያበረክት መሪዎቿ በፍጹም ቅንነትና ኃላፊነት እንዲሠሩም አሳሰበዋል።

የቀድሞ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አባዱላ ገመዳ በበኩላቸው፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለዘመናት በብዙ መልኩ አስከፊ ድህነት ውስጥ እንደነበሩ አውስተው፤ በተለይ በአካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች በአዲስ አበባ አፍንጫ ስር ሆነው ማገዶ እየሸጡ ኑሮ እየገፉ መሆናቸውን አንስተዋል።

አብዛኞቹ አርሶ አደሮች ተገፍተው ከቀያቸው ተፈናቅለዋል ያሉት አባ ዱላ፤ የቀሩትም ቢሆኑ የትምህርት ደረጃቸው ከመሐል አገር ርቀው ከሚኖሩት ከአርብቶ አደር የኅብረተሰብ ክፍሎች በታች መሆኑን አስገንዝበዋል።

የአካባቢው መሠረተ ልማት ዝርጋታና የሥራ እድል ፈጠራም እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን የአካባቢውን ችግሮች ብሎም ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገትና ማኅበራዊ ትስስር ሸገር ቁልፍ መፍትሔ ነው ብለዋል።

ከተማዋ በዚህ መልኩ መመስረቷ ከኅብረተሰቡም አልፎ ለሀገርም ያለው ፋይዳ የጎላ ይሆናል ብለዋል።

የከተማዋ ከንቲባ ዶክተር ተሾመ አዱኛ፤ የሸገር ከተማ ምሥረታ እውን እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላበረከቱት አካላት አመስግነው፤ በከተማዋ ሁለንተናዊ እድገት ለማምጣት በኃላፊነት ስሜት እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

ለቀድሞዎቹ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንቶችና ለከተማዋ ምሥረታ አስተዋፅዖ ላበረከቱት ግለሰቦች በአቶ ሽመልስ አብዲሳ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

## ባለፉት ሰባት ወራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶላር ተገኝቷል።

181 ሺ 323 ነጥብ አምስት ቶን በመላክ በገቢ 867 ነጥብ ሰባት ዶላር ለማግኘት ታቅዶ እንደነበርም አመልክተዋል።

ገቢው ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የገቢ መጨመር ሲያሳይ፣ በመጠን አንጻራዊ ቅናሽ ማሳየቱንም ነው የገለጹት።

በመጠን የቀነሰው የቡና ምርት የሚጠናቀቅበት ወቅት፣ የባለፈው ምርት ተሟጥጦ ከቡና ላኪዎች የሚወጣበት እና አዲሱ ምርት ደግሞ ከአቅራቢዎች ተዘጋጅቶ ወደ ላኪዎች የሚገባበት የጊዜ ክፍተት ላይ በመሆኑ ነው ብለዋል።

አብዛኛው የታጠበ ደረቅ ቡናም ከአቅራቢዎች ተሰብስቦ ከመጋዘናቸው ወደ ላኪዎች በሽያጭ የሚተላለፍበት ወቅት ከተያዘው ወር በኋላ መሆኑንም አመልክተዋል።

አብዛኛውን ጊዜ ከጥቅምት እስከ ጥር ያለው ጊዜ ቡና በባሕሪው በአቅራቢዎች እጅ የሚዘጋጅበት እና የሚታጠብበት ጊዜ ነው።ሂደቱ ወደ ላኪው ለመድረስ የተወሰነ ጊዜ ይፈልጋል ብለዋል።

አሁን የዝግጅት ወቅቱ አብቅቶ አቅራቢዎች ከላኪዎች ጋር የሚገናኙበት የግብይት ጊዜ ነው።የመጠን ቅናሹ ከዚህ ጊዜ በኋላ እንደሚስተካከል ይጠበቃል ነው ያሉት አቶ ቸሩ።

ባለፉት ሦስት ዓመታት የኢትዮጵያ ቡና በጥራት ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል ያሉት አቶ ቸሩ፤ ከዚህ በፊት ግብይቱ አቅራቢው ደስ ያለውን አዘጋጅቶ ያቀረበውን፣ ላኪውም ይሆነኛል የሚለውን ገዝቶ የሚልክበትና ትኩረቱም መጠን ላይ እንደነበረም ነው ያስታወሱት።

አሁን የዓለም አቀፍ ገበያ መጠንን ሳይሆን ጥራትን የሚያበረታታ በመሆኑ ጥራት ላይ ትኩረት እንዲደረግ፤ ከአርሶ አደሩ ጀምሮ ባለድርሻዎች፣ አቅራቢዎች እና ላኪዎችን በማሳተፍ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በስፋት መሠራቱን ነው የገለጹት።

ባለፉት ሦስት ዓመታት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በቡና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት፤ አርሶ አደሮች፣ አቅራቢዎች እና ላኪዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉንም ነው ያመለከቱት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ትግበራውም ለውጦች አሳይቷል። ከ2014 ዓ.ም ከተላኩ ጠቅላላ ምርቶች 70 ከመቶ ያለው ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት ያለውን የሚይዝ ነው። ዘንድሮም 80 በመቶ የሚሆነው ምርት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት እንዲሆን ታቅዶ ለማሳካት እየተሠራ ይገኛል።

በአቅራቢዎች በኩል ያለፉት ዓመታትን ተሞክሮ ተመልክቶ የዓለማቀፍ ገበያን ከግንዛቤ ሳያስገቡ በታጠበም ሆነ በደረቅ ቡና ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ዋጋ ሰቅሎ መግዛት፣ ላኪዎች ምርቱን የሚሸጡት ከፍተኛ የማምረት አቅም ካላቸው ከእነ ብራዚል፣ ቬይትናምና ኮሎምቢያ ጋር በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ነው።

በመሆኑም ንጽጽሩ በኒውዮርክ ገበያ በየዕለቱ ባለው እንቅስቃሴ የአቅራቢውን ያክል ዋጋ ያለመድፈር ከዘርፉ ውስንነቶች ጠቅሰዋል።

በዋናነት በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያን የቡና ምርት የሚገዙ ሀገራት ዓረብ ሀገራት ናቸው። ልዩ ቡናዎች የሚላኩት ደግሞ ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካና የተለያዩ ሀገራት መሆናቸውን ነው የገለጹት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎቻችን በተሻለ መልኩ ውጤታማ እንዲሆኑ!

ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎች ከፍያለ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ኢኮኖሚያቸውን በግብርና ላይ መሰረት ላደረጉ አገራት ትልቁ የቤት ስራ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ነገዎቻቸውን ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ተስፋ አድርገው ለሚንቀሳቀሱ ሕዝቦች ጉዳዩ የህልውና ያህል አደጋ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

እነዚህ ሕዝቦች በትንሹ የእለት ምግባቸውን አምርተው፤ ዛሬን ለመሻገር በተፈጥሮ ሀብታቸው /በአፈር፣በአየር እና በውሀው/ ላይ ያላቸው ቁርኝት የህልውናቸው ያህል ነው። ይህም ለተፈጥሮ ሀብታቸው ሊሰጡት የሚገባው ትኩረት የቱን ያህል ወሳኝ እንደሆነ አመላካች ነው።

እንደ ሕዝብ ዛሬ ላይ በዘርፉ የሚፈጥሩት መዘናጋት ከነሱ አልፎ መጪዎቹን ትውልዶ ቻቸውን የከፋ አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል፤ ጊዜው ካለፈ በኋላ ከችግሩ ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረትም ያልተገቡ ዋጋዎችን ከመክፈል መታደግ የሚያስችል አቅም ሊኖረው አይችልም።

በእኛም አገር ቢሆን ከግንዛቤ እጥረት ምክንያት የቀደሙት ትውልዶች በተፈጥሮ ላይ ካደረሱት መጠነ ሰፊ ውድመት የተነሳ፤ አሁን ያለው ትውልድ ከፍ ያሉ ዋጋዎችን ለመክፈል ተገድዷል፤ እየተገደደም ነው።

ለዚህም ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ በአገሪቱ በየአስር ዓመቱ እየተከሰቱ ያሉ፤ የድርቅ አደጋዎች እና እያስከተሉት ያለው ጥፋት የዚሁ እውነታ አንድ ተጨባጭ ማሳያ ናቸው። ዛሬም በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚሰማው የድርቅ እና የድርቅ አደጋ ወሬ የዚሁ እውነታ አንድ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ይህንን ተጨባጭ እውነታ በአግባቡ በመረዳት አገራችንም ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዙሪያ ሰፊና ቀጣይነት ያላቸው ስራዎች ሰርታለች፤ በዚህም ከፍተኛ መጠን ያለው የተፈጥሮ ሀብት እንዲያገግም በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ተጠቃሽ ልትሆን ችላለች።

በተለይም በተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች ስር አርሶ አደሮችን በስፋት በማሳተፍ ሰፊ መሬት እንዲያገግም አድርጋለች። በዚህም የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል ባለፈ ለግብርና ስራዎች ምርታማነት የተሻለ አቅም መፍጠር ችላለች።

በአሁኑ ሰአት በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝባችን እያስገኘለት ካለው ጠቀሜታ አንጻር፣ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራዎች ላይ የመሳተፍ የደን ችግኞችን የማልማትና የመጠበቅ ባህሉን እያዳበረ መጥቷል።

ከዚህ ጎን ለጎንም ለእንስሳት መኖና ለምግብ ፍጆታ የሚውሉ ችግኞችን በመትከል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራው የበለጠ በህይወቱ ትርጉም እንዲኖረው እየሰራ ነው። ይህም የተጠቃሚነቱን ደረጃ እያሳደገው ይገኛል።

ይህም ሆኖ ግን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በአሁኑ ወቅት ሰባት ሚሊየን ሄክታር መሬት በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ ነው፤ ከዚህ ውስጥ ሶስት ሚሊየን ሄክታር መሬቱ የአሲዳማነት ደረጃ ከፍተኛ ነው።

በተለይ ትርፍ አምራች ከሚባሉት ክልሎች በምዕራብ አማራ፣ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች የአፈር ሆምጣጤነት በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

ይህ ከደን መመናመን /ጭፍጨፋ/ ጋር በተያያዘ እየተከሰተ ያለ ችግር፤ ምርታማነት ላይ ከሚያሳድረው ተጽእኖ ባለፈ፤ በቀጣይ በምግብ እህል እርሳችንን ለመቻል ለምናደርገው ጥረት ስኬት ዋነኛ ተግዳሮት መሆኑ የማይቀር ነው።

ችግሩን ለመቅረፍ በዋነኛነት በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እየሆነ ያለውንና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያተረፈውን የአረንጓዴ አሻራ መስፋት ማስቀጠል ያስፈልጋል፤ ቀደም ብለው የተጀመሩ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

በተለይ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎችን በተሻለ መልኩ ውጤታማ እንዲሆኑ፤ ሥራውን አገራዊ ንቅናቄ አድርጎ ማስቀጠል ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የፖለቲካ አመራሩን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ ወሳኝ ነው!

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
• ወርቁ ማሩ
• ኃይሉ ሣህለድንግል
• አልማዝ አያሌው
• እስማኤል አረቦ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትምህርት ጥራትና ችግሮችን ለመቅረፍ ከማን ምን ይጠበቃል?

**መምህር አረሩ አዱሳ**

የአገራት እድገት ዘላቂነትና አስተማማኝነት የሚረጋጋጠው ባላቸው እምቅ የተፈጥሮ ሀብት አልያም ባከማቹት የጦር መሳሪያ ልክ ሳይሆን ባላቸው የማህበረሰብ ንቃተ ህሊና ደረጃ ነው። ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ ንቃተ ህሊና መበልጸግ ደግሞ ትምህርት ዋነኛ መሳሪያ ነው።

ትምህርት ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ ብሎም በአገረ አቀፍ ደረጃ ለሚመዘገቡ የኢኮኖሚ እድገት ሰላምና ብልጽግና ዋነኛ መንገድ ነው። በቅርቡ የዓለም ታሪክ የምናስታውሳቸው ከነዳጅ እስከ የከበሩ መአድናት በጉያቸው ታቅፈው በምድራቸው ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎችን የያዙና በውስጥ ችግሮቻቸው እየታመሱ ያፈሩትን ጥሪታቸው በጦርነት ያወደሙ አገራት ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ናቸው።

ትውልድ የሚቀረጸው በትምህርት እንደመሆኑ በትውልድ ላይ የማይሰራ አገርም ካለመበት የመድረሱ ጉዳይ አጠራጣሪ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም ነው። ይህን እንደመንደርደሪያ ያስቀመጥኩት በቅርቡ የተማሪዎችን ውጤት አስመልክቶ ስለተለቀቁት ዜናዎችና ስለተባሉት ሁሉ አንዳንድ ነገር ለማለት ስለወደድኩ ነው።

በቅድሚያ 2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት (666) በማስመዝገብ ካመጣው የደሴ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ አድናቆቴን እየገለፅኩ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለሚገቡት ዕድሉ የገጠማችሁን ሁሉ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ። ተፈትናችሁ ለጊዜው ወጤት ያላመጣችሁ ነገ ሌላ ቀን መሆኑን ተረድታችሁ በአዲስ ሞራል፣ የስነ ልቦና ዝግጅት አይቻልም የሚለውን ተስፋ አስቆራጭ ሃሳብ ከአእምሯችሁ ገለል ማድረግ ይጠበቅባችኋል። ለቀጣይም ከአለፈው ስህተቶቻችሁ በመማርና በርትቶ በመስራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የማትቀላቀሉበት አንዳችም ምክንያት አይኖርምና በርቱ ለማለት እወዳለሁ፡፡

ወደዋናው ጉዳዩ ስገባ ግን የትምህርት ጥራት መጓደልም ሆነ የተማሪዎች ፈተና መውደቅ የልጆቹ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ችግር እንደመሆኑ ሁሉም በየደረጃው ኃላፊነቱን መውሰድ ብሎም ለማስተካከል የሚጠበቅበትን መወጣት እንዳለበት ይሰማኛል። በመሆኑም በአገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆልና የትምህርት ጥራት አለመምጣት ዋነኛ ተጠያቂ ናቸው የምላቸውን ከሚጠበቅባቸው ተግባር ጋር እንደሚከተለው ለማቅረብ እወዳለሁ።

በመንግስት በኩል ያለውን የትምህርት ጥራት ችግሮች በማጥናት ሰፊ ክትትል በማድረግ መፍትሔ መስጠትና በየአካባቢው ያሉ የሰላም ችግሮችን በወቅቱ መፍታት። ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፖሊሲና እና ስርዓተ ትምህርቱን የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘቡና ችግር ፈቺ ብሎም ስራ ፈጣሪ ትውልድ የሚያፈሩ እንዲሆኑ ማስቻል። የትምህርት ባለድርሻ አካላት የሚባሉትም ሁሉም በአንድነት በመቆም አገራዊ እሳቤን በመያዝ ለአጠቃለይ የመማር ማስተማሩ ሂደት እኩል በመነሳት በህብረት መስራት።

የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ዘወትር ራሳቸውን እያበቁና ከግዜ ጋር እየተራመዱ ተቋሞቻቸውን በብቃት ማስተዳደር። በትክክለኛው፣ ሰዓት፣ ጊዜ፣ ቦታ በመገኘትና ከሙስና በቡድን ከማሰብ፣ ከጎጠኝነት፣ ከብሄርተኝነት፣ ከመንደርተኝነት፣ ፅንፍ መውጣት ይጠበቅባቸዋል። እያንዳንዱ መመህር በቅድሚያ ለሙያው ፍቅር ኖሮት ራሱን በስነ ምግባር በማነፅና በየጊዜው በማብቃት ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለፈጠራ ምርምር በመዘጋጀት ትውልድ አሻጋሪ ዜጋ በእውቀት ለመፍጠር መነሳት፡፡ የፈተና በሚወጣበት ወቅትም ሆነ የፈተና አሰጣጣ ተማሪውን በዕውቀት መገንባት የሚያችል ደንብና የፈተና ህጉን የተከተለ ማድረግ፡፡

የመምህራን ማህበራት አሁን ለተፈጠሩት ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች መፍትሄና ምላሽ ከመስጠት አኳያ እየሰሩት ስራ የሚበረታታ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ

**ከሁሉምና ከምንም በላይ እያንዳንዱ ቤተሰብ ልጁን ወደትምህርት ገበታ ለምን እንደሚልክ ማወቅ፤ አውቆም መከታተል ይጠበቅበታል።**

የተወከሉበትን ኃላፊነትና ተግባር ቅድሚያ በመስጠት በመምህሩ የሚቀርቡ አያሌ ችግሮች በየደረጃቸው መፍትሄ እንዲያገኙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተማሪው ከሁሉም በላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ትልቁ የተማሪ ድርሻ መማር መሆኑን ተገንዝቦ ለትምህርቱ ሰፊ ዝግጅትና ጥናት በማድረግ ሌት ከቀን ቤተሰብና ማህበረሰቡ በሚጠበቅበት ስነምግባር በመታነፅ ኩረጃን በመጥላት በአላማ እና ዕቅድ በመስራት ለሚጠበቅበት ራሱን አሳልፎ መስጠት ይገባዋል ፡፡

ማህበረሰቡ ትምህርት ቤቶችንና ተማሪዎችን የራሱ ሀብቶች መሆናቸውን በመገንዘብ እና በመረዳት ከመንግስት፤ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት የትምህርት ቤቶችን አቅም ማጎልበትና ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ ለሚደረገው ርብርብ የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል።

ከሁሉምና ከምንም በላይ እያንዳንዱ ቤተሰብ ልጁን ወደትምህርት ገበታ ለምን እንደሚልክ ማወቅ፤ አውቆም መከታተል ይጠበቅበታል። በየእለቱ የልጆቹን ውሎ ከመከታተል ባለፈም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መወያየትና ክትትል ማድረግ አለበት።

ባጠቃላይም በአገራዊ ዕሳቤዎች ኢትዮጵያውያን ዲያስቦራዎች፣ አክትቪስቶች፣ በጎ አድራጊ ተቋማት የሚታየውን የትምህርት ጥራት ችግር፤ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩትን ችግሮች ቀድሞ በመረዳት አገራዊ ኃላፊነትን በመውሰድ የግል የጋራ ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። በመጨረሻም ትምህርትን በብቃትና በጥራት ለሁሉም የምናደርገው ስራ ሀሳብ ከወረቀት በዘለለ ወደ መሬት ለማውረድ ተግባራዊ ለማድረግ ሁላችንም እንነሳ እላለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሁለቱ የባህል ፋሽን አርበኞች

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያ በፋሽን ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የምትችልበት ሰፊ እድል ነበራት። ነገር ግን ነገሩ በነበር ቀረና በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ተወዳዳሪ መሆን ሳትችል ቀርታለች። ለዚህም ሁለት አበይት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው ያለንን አገራዊ እምቅ ሀብት አለማወቃችን ነው። ያወቅነውን አለመጠቀማችን ደግሞ ሌላው ሲሆን የመጀመሪያውን ግንብ ደርምሰው የሚገቡ ቆራጥ ፈተኞች ባለመኖራቸው ነው።

አሁን አሁን ግን ሁሉም ነገር እየተቀየረ የመጣ ይመስላል። በዘመናዊው የፋሽን ኢንዱስትሪ ሰቅዞ ከያዘን አባዜና ድንዛዜ ነቅተው የሚያነቁ የፋሽኑ ዓለም ጀግኖች ከየአቅጣጫው እየወጡ ወደ ውድድሩ ሜዳ መትመም ጀምረዋል። ከእነዚህም መካከል ስለ ሁለቱ የኢትዮጵያ የዘመናዊ ፋሽን የፊት ደጀን አርበኞች ጥቂት ነገር እንበል።

በፋሽን ኢንዱስትሪው ምንም ከማይታይበት ድንግዝግዝ ጨለማ በድፍረት ዘልቃ በመግባት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የበቃችውና የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የዘመናዊ ፋሽን ድልድይ መሆን የቻለችው ጀግና አርበኛ ዲዛይነር ገነት ከበደ ናት። ከ30 ዓመታት በፊት ገነት ፓራዳይዝ የተሰኘውን ድርጅት መስርታ የኢትዮጵያን የባህል አልባሳት በዘመናዊ መንገድ እያዘጋጀች ለዓለም አቀፍ ገበያ ታቀርባለች። በዓለማችን ከፍተኛ ነዋይ በሚፈስበት የፋሽን ኢንዱስትሪ ውስጥም ተቀባይነትን ማግኘት ችላለች። በተለይ የምትታወቅበት ደግሞ በባህላዊ የሽመና ውጤቶች ዘመናዊ የሙሽራ እና የሚዜ አልባሳትን በመስራት ነው።

ኢትዮጵያዊቷ እውቅ ዲዛይነር ገነት ከበደ የፋሽን ጥበብን በጣሊያን እና አርጀንቲና ተምራ ወደ አገሯ ትመለስ እንጂ፣ ለፋሽን እና ለዲዛይን ጥበብ ያላት ፍቅር የሚጀምረው ገና ከልጅነቷ ነው። በአሁኑ ሰዓትም ገነት ፋሽን በሚል ስያሜ የሚታወቁ የተለያዩ በባህላዊ ጨርቆች የተሰሩ አልባሳት በገበያ ላይ ይገኛሉ። የሽመና



**ዲዛይነር ገነት ከበደ፣**



**ሞዴልና ዲዛይነር ሰናይት ማሪዎ፣**

ጨርቆች በዘመናዊ መልክ በስፋት እንዲመረቱ እና ለገበያ እንዲቀርቡ የማድረግ ሂደቱ ተጀመረ እንጂ ገና ምኑም አልተነካም በማለትም ትናገራለች።

በዚህ ዘርፍ ውስጥ እሷና እሷን መሰል ጥቂት ዲዛይነሮች ብቻ የኢትዮጵያን የፋሽን ኢንዱስትሪ ለማሳደግ በቂ እንዳልሆኑ የምታምነው ገነት፣ ያላትን እውቀትና ልምድ ለሌሎች ለማካፈል የማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የመክፈት ትልቅ ህልም አላት። ስራዎቿን እና በዘርፉ ያበረከተችውን አስተዋፅኦ የሚዘክር ታላቅ የፋሽንና የሙዚቃ ትርዒት በየጊዜው ይዘጋጃል። ከዚህ የፋሽን ትርዒት የሚሰበሰበው ገቢም በካንሰር በሽታ ለተጠቁ ህፃናት ህክምና ይውላል።

ሌላኛዋና የኢትዮጵያ የዘመናዊ ፋሽን የፊት ደጀን አርበኛ ደግሞ የዊን ፒስ መስራቿ ሞዴልና ዲዛይነር ሰናይት ማሪዎ ናት። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትልም በትጋትና ጥረት የፋሽን ኢንዱስትሪው አንድ እርምጃ ወደፊት እንዲሄድ አድርጋዋለች። ዊን ፒስ የተሰኘውን ድርጅት በማቋቋም የኢትዮጵያን የባህል አልባሳት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የማድረግ ራዕይ ሰንቃ በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ በመንቀሳቀስ ትታወቃለች። ሞዴልና ዲዛይነር ሰናይት እንዴት ወደዚህ ሙያ እንደገባች ስትናገርም “በአንድ ወቅት ጣሊያን አገር ነበርኩኝ፣ በዚያ ሰዓት ሙያውና እውቀቱ እንዳለኝ ባስብም በትንሹ ከመሞካከር ውጭ እዚህ ደረጃ ላይ ግን እደርሳለሁ ብዬ አንድም ቀን አስቤ አላውቅም ነበር። ታዲያ ሁል ጊዜ በጣሊያን ጎዳናዎችና በሄድኩባቸው ቦታዎች ሁሉ አለባበሴን፣ ቁመቴን፣ እንዲሁም የሀበሻ መልኬን የተመለከቱ ሞዴል ነሻ?...ግን ለምን ሞዴል አትሆኚም?... የሚሉኝ ሰዎች በዙ። እኔም ያለኝን ነገር ትልቅ ደረጃ ላይ ማድረስ እንደምችል አመንኩ።” በማለት ትገልጻለች።

ገና ወደስራው ሳትገባ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትና የሞዴልነትን ማዕረግ ያገኘችው ሰናይት፣ ጊዜዋን ሳታባክን ወዲያው ወደ ሞዴሊንግ ሙያ ገባች። ለተወሰኑ ዓመታትም ስኬታማ ሊባል በሚችል መልኩ በዚያው ሙያ ቆይታ ከዚያም ወደ ዘመናዊ የፋሽን ኢንዱስትሪ በዲዛይነርነት ተቀላቀለች። ሁለቱም ሙያዎች ተያያዥ ቢሆኑም ወደ ሁለተኛው ሙያ እንድታደላ ያደረጋት አንድ ጉዳይ ገጥሟት ነበር። በወቅቱ ሰናይት የልጅ እናት ሆነችና ለተወሰኑ ጊዜያት ከሞዴሊንጉ በመራቋ የሰውነት ቅርጿም ከሞዴልነት ዓለም ቀስ በቀስ እያሸሻት እንደሆነ ተመለከተች። ወደ ፋሽን ዲዛይነርነት ብትገባ ስኬታማ መሆን እንደምትችል ስለተረዳችም ከሞዴልነት ወደ ፋሽን ዲዛይነርነት ቀየረች። ሌላው እንደ ምክንያትነት የምታነሳው ሞዴል በነበረችበት ወቅት ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ጋናና ሌሎችም የአፍሪካ አገራት የባህል አልባሳቶቻቸውን ለዓለም ገበያ ሲያቀርቡ ትመለከት ስለነበረ ኢትዮጵያስ ከእነርሱ የተሻለ አገራዊ ሀብት እያላት በፋሽን ኢንዱስትሪው ለምን የበታች ሆነች? የሚል ቁጭት በውስጧ ማደሩን ትናገራለች።

አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት የባህል አልባሳቶ ቻቸውን ሰርተው ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ጥሬ እቃውን የሚወስዱት ደግሞ ከኢትዮጵያ ነበር። ይባስ ብሎም መልሰው የሚሸጡት ለእኛው ነው። ይህም መንፈሳዊ ቅናት ስላሳደረባት አይኗን ሳታሽ በቀጥታ ወደሙያው ገባችበት። በአንድ ወቅት አንድ ልብስ ነጮቹ ለብሰውት ሲታዩ በማህበራዊ ሚዲያዎች ብዙዎች እየተቀባበሉም በአድናቆት ብዙ ነገር ብለውለታል። በነጮች ስላዩትም የጀርመን ባንዲራ የሚመስላቸውም ነበሩ። ነገር ግን ልብሱ ከወላይታ ‘ድንጉዛ’ የተሰራ፣ ፈጠራውም የዲዛይነሯ ሰናይት የመጀመሪያ ስራ ነበር። ዊን ፒስ ፋሽንን ለመመስረት አቅሙን ያገኘችውም ከዚህ በኋላ ነበር። በፈጠራዎች የተካነችው ዲዛይነሯ ከእንስት በአልኮል ታጥበው ከድንች ጋር በመቀላቀል በርካታ ስራዎችን መስራት ችላለች። በአሁኑ ሰዓትም የተለያዩ የአገር አልባሳትን በመስራት ለዓለም አቀፍ ገበያ ታቀርባለች። ፓሪስ፣ ሚላን፣ ኒውዮርክ፣ ከአፍሪካ ደግሞ ጋና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያን ጨምሮ በተለያዩ አገራት በመዘዋወር ስራዎቿን ለማሳየት በቅታለች። በምታደርገው እንቅስቃሴም በናይጄሪያ፣ ጋና፣ አሜሪካና በኢትዮጵያ አቢሲኒያ አዋርድ ላይ የተለያዩ ሽልማቶችን አግኝታለች፡፡

የእነዚህ የዘመናዊው ፋሽን የፊት ደጀን፣ ጀግና አርበኞች አገራችን ኢትዮጵያ በባህላዊው የፋሽን ዓለም የነበራትን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ይታገላሉ። እኛም የእነርሱን አርአያነት እንከተል። ሰጪዎች እንጂ ተቀባዮች እንዳንሆንም፣ ለአገራችን የፋሽን ኩራት ዋልታ እንቁም።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## «ቲፕ» መስጠት ግዴታ ነው?

**ቦጋስ አበበ**

ጉርሻ ወይም «ቲፕ» እንግዶች/ተገልጋዮች በሆቴል ወይም በማንኛው የአገልግሎት መስጫ ማዕከል ውስጥ መልካም አገልግሎት(መስተንግዶ) የቀረበላቸው እንደሆነ በፈቃደኝነት የሚሰጡት የማትጊያ ጉርሻ ነው። ቲፕ በስፋት እንደሚስተዋለው በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ ነው፡፡

ቲፕ በሆቴል አገልግሎት ሰጪ ከሆኑ ሰራተኞች መካከል በስፋትና በተለመደው መልኩ ለምግብ ቤት አስተናጋጆችና ለእንግዳ መቀበያ ክፍል ሰራተኞች( እንግዳ ተቀባዮች) ይሰጣል፡፡ ለዚህ ዋነኛ ምክንያት፣ እንግዶች (ደንበኞች) የምግብ ቤት አስተናጋጆችን በፊት ለፊት ስለሚያገኙያቸውና ቀጥተኛ መስተንግዶ ከእነርሱ ስለሚያገኙ ነው፡፡ በተለይ ደንበኞች ወደ ሆቴል የሚሄዱት የማደሪያ አገልግሎት ለማግኘት ከሆነ በቅድሚያ የሆቴሉን ገፅታ የሚያገኙት ከእንግዳ ተቀባዮች ነው፣ በመቀጠልም የቆይታቸውን ረጅም ጊዜ የሚያሳልፉት በምግብ ቤት አካባቢ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የስራ ክፍሎች በተደጋጋሚ እንግዶችን የማግኘትና የመርዳት አጋጣሚያቸው በጣም ከፍተኛና የስራቸው ዋና አላማ ነው፡፡

ቲፕ ለአሰሪ ድርጅቶችና ለተቀጣሪ ሰራተኞች ሰፊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ቲፕ በቀጥታ የሚያገኘው ግለሰብ የገንዘብ አቅሙን ከፍተኛ ያደርግለታል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም ቲፕ የሚያገኙ አስተናጋጆች በተለየ ሁኔታ ፈጣንና ታዛዥ ናቸው ተብሎ ይታመናል። በሌላ መልኩም ቲፕ የሰራተኞችን የመስራት መንፈስ ያነቃቃል፣ ያወዳድራል፣ የህብረት ስራዎችን ያቀጣጥላል፣ በሰራተኞች መካከል የመተጋገዝ መንፈስ ይፈጥራል ይባላል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው መልኩ ግን ቲፕ በአግባቡ ያልተያዘና ወጥ ስርዓት የሌለው እንደሆነ ለሰራተኞች ከሚያስገኘው የገንዘብ ጠቀሜታ በዘለለ ሌላ ፋይዳ አይኖረውም፣ እንደውም የፉክክር ባህሪያት፣ ያለመተማመን፣ የአድሎት፣ የልግመኝነት፣ የስራ መርጫ ሁኔታዎችን ያስፋፋል፡፡ ቲፕ ለሁለቱም ወገኖች ተቀሜታ እንዲኖረው ለማድረግ በአንዳንድ ሆቴሎችና ማግብ ቤቶች የሚደረጉ ልማዶች አሉ፡፡ እነዚህ ልማዶች ለሃገራችን የሆቴል ተጠቃሚና ሰራተኞች ያልተለመዱ ይሁኑ እንጂ በሌሎች አለማት መደበኛ አሰራር ናቸው፡፡

ለምሳሌ ያህል ቲፕ ለሁሉም በሚል መርህ አሰሪዎች (ሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶች) የቲፕ መሰብሰቢያ አንድ ሳጥን በማዘጋጀት ለደንበኞች መስተንግዶ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሰራተኞች እንዲከፋፈሉት ያደርጋሉ። ለምሳሌ ቲፕ የተሰበሰበው በምግብ አዳራሽ ከሆነ፣ የምግብ ዝግጅት ሰራተኞች፣ የምግብ ቤት ፅዳት ሰራተኞች፣ ዕቃ አጣቢዎች፣ አስተናጋጆች፣ ባር ሰራተኛ፣ ካሸር እና ሌሎች ለምግብ መጠጥ መስተንግዶ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ሰራተኞች በተለያየ ኮታ መሰረት እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፡፡ ይህን አሰራር በውጪ አለም በጣም የተለመደ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ የውጭ ሃገር ጎብኚዎች ቲፕ ከመስጠታቸው በፊት ይህንን ሳጥን ይጠይቃሉ፡፡

በኢትዮጵያ በቲፕ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ይነሳሉ፡፡ ቲፕ የሚሰጠው ለትላላቅ ሆቴሎች ሰራተኞች ብቻ ነው፣ የቲፕ መጠን ስንት ነው፣ ቲፕ መስጠት ግዴታ ነው የሚሉና ሌሎችም ናቸው፡፡ ቲፕ የእንግዶች በጎ ፈቃድ ነው፡፡ ቲፕ እንግዶች ለተደረገላቸው መልካም መስተንግዶ የማበረታቻ ስጦታ ነው፣ ቲፕ በእንግዶች አቅም መሰረት መሰጠት ያለበት ስጦታ መሆን አለበት፡ ፡ ለውጭ ሃገር ዜጎች በሚታተሙ የጉዞ መጠቆሚያ ሰነዶች ላይ (GUIDE BOOK) ቲፕ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ግምት ያለው መሆኑንና የቲፕ አሰጣጥ በሆቴሎች ውስጥ ሊሰጥ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የቲፕ መጠን በሆቴሎች ደረጃ ሊለያይ እንደሚችልም ያስረዳል፡፡

እኛ ጋር ግን ጉዳዩ ተቃራኒ ሆኖ ይታያል። በቲፕ ተቀባይ ሰራተኞች የቲፕ ጠባቂነት (ለቲፕ መቁለጭለጭ) አንዱ ነው፡፡ በብዛት ሰራተኞች እንግዶችን የሚያስተናግዱት ቲፕ እንዲሰጣቸው ነው፡፡ እንግዶችን የሚያስተናግዱት ድርጅቱ በገንዘብ በቀጠራቸው ደሞዝ መሆኑን ማሰብ አይፈልጉም፡፡ ያው የሚከፈላቸው ደመወዝ ትንሽ ከመሆኑም ጋር ተያይዞ ሊሆን ይችላል፡፡ ቲፕ የመልካም መስተንግዶ ማበረታቻ መሆኑን ያለመረዳት ችግርም በስፋት ይታያል፡፡

የደንበኞች የክፍያ ቀሪ ገንዘብ ማረሳሳት፣ ደንበኞች ከመስተንግዶ በኃላ ክፍያ ፈፅመው ተመላሽ ገንዘብ ሊኖራቸው ችላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የደንበኞችን ገንዘብ በፍጥነት ባለመመለስ ወይም ዝርዝር የለም በማለት የእንግዶችን መልስ ለማስቀረት መሞከር ሌላው ችግር ነው፡፡ መልስ የግድ መመለስ ካለባቸውም ለቲፕ እንዲመች በማድረግ ዝርዝር ሳንቲም መስጠት የተለመደ ነው፡፡

አድሎ ማድረግ ሌላው ጉድለት ነው፡፡ ሰራተኞች በተደጋጋሚ ቲፕ የሚሰጣቸውንና የማይሰጣቸውን ተገልጋይ በመለየት አድልዎ ማድረግ ከፍተኛ የስነ ምግባር ጉድለት ሲፈፅሙ ያልገጠመው አለ?፡፡ አድሎ በዚህ ብቻ አይገለፅም ቲፕ የሚሰጡና የማይሰጡ ብሎ እንግዶችን በቅድሚያ መገመትና መጠበቅ ባህሪም ይስተዋላል፡፡

ቲፕ ግዴታ ነው ብሎ ማሰብ፣ እንግዶች ቲፕ የመስጠት ግዴታ የለባቸውም፡፡ ቲፕ የሚሰጡት በፈቃደኝነት ነው፣ በመሆኑም እንግዶች ቲፕ እንዲሰጡ መገፋፋትና አስገዳጅ ሁኔታዎችን መደርደር ተገቢ አይደለም፡፡

ቲፕ የሚሰጣቸው ሰራተኞች ለእንግዶች በሰጡት መስተንግዶ የራሳቸው ብቻ ጥረት አይደለም፣ ሌሎች ለእንግዶች ያልታዩ ነገር ግን ለምግብ መጠጥ ይሁን ለሌላ መስተንግዶ የሚለፉ ሰራተኞች ከጀርባ አሉ፣ እነዚህን ሰራተኞች ለማካፈልና ለማበረታት ማድረግ የሚችል ቲፕ ተቀባይ አይስተዋልም፡፡

ቲፕ ተቀባዮች ዛሬ ላይ ቲፕ ከሚያገኙበት የስራ ዘርፍ ላይ ወደ ሌላ የስራ መስመር ለመሄድ ፍላጎት ያለማሳየትም አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቲፕ ተቀባዮች ሊያስቡት የሚገባ ጉዳይ መጪው ዘመን ለቲፕ የተመቸ አለመሆኑን ነው፡፡ ቴክኖሎጂ በተስፋፋ ጊዜ የክፍያ ስርዓት እጅግ በተራቀቀና ካሽ በሌለበት መሆኑ አይቀሬ ሲሆን በመመልከት ላይ ነን፡፡ ለምሳሌ ቲፕ በቻይና ክልክል ነው፤ እንደውም ሆቴሎች “ቲፕ ክልክል ነው” ብለው ማስታወቂያ በምግብ ቤታቸው የሚለጥፉም አሉ፡፡

ቲፕ ማግኘቱ ጥሩ ነው፡፡ ቲፕ መልመዱ ግን በጣም አደገኛ ልማድ ነው፡፡ የቲፕ ሱስ የሚመስል ልማድ ያለባቸው ሰራተኞች ዛሬም ቲፕ በማሳደድ ከፍተኛ የስራ ሃላፊነትን የሚሸሹ ቤት ይቁጠራቸው፡፡ ቲፕ ዘወርት ጠባቂነትን መንፈስ ይፈጥራል፣ ገንዘብ በቀላሉ የማግኘት አባዜን ያዳብራል፡፡ የቲፕ ሱስ አደገኛ ነው፡፡

## ነፃ ሃሳብ

# በመሸነፍ፣ ማሸነፍን፤ በመተው፣ ማትረፍን፤ በይቅርታ፣ መራመድን፤ ...

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ጦርነትን እንደ ትልቅ የሰላም ምንጭ ስትጠቀመው ቆይታለች። ያለፉትንም ሆነ የቅርብ ጊዜ የጦርነት ትዝታዎቻችንን መለስ ብለን ብንቃኝ አገር ከማውደም ባለፈ ያተረፉልን አንዳች ነገር እንደሌለ እንደርስበታለን። እያንዳንዱ አገራዊ ጉዳያችን ለጦርነት በር ከፋች ከመሆኑም በላይ የመፍትሄ ሀሳቦችን መለስ ብለን እንዳናይ ያደረገም ነበር።

ከሁሉ በላይ በፖለቲካው ምህዳር የተለማመድናቸው አጉል ልምምዶች የሰላም አማራጮችን እንዳናይ ከማድረጋቸውም ባለፈ ለጦርነት መንገድ የሚጠርጉ እንደነበሩ ትላንትን ማስታወሱ በቂ ነው። የአሁኗን ኢትዮጵያ ጠፍጥፈው ያበጁት እነዚህ ለሰላም የሚሆን ልዕልና የሌላቸው አስተሳሰቦች ናቸው ።

ከትላንት እስከ ዛሬ እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል እሳቤ አሸናፊ በሌለው የብኩርና ግፊያ ለንክሻና ለመለያየት ተዳርገናል። ሀሳብን በሀሳብ ማሸነፍ ተስኖን፣ ልዩነትን በጋራ እውነት መርታት አቅቶን ቅራኔዎቻችንን ሁሉ ወደ ጦርነት ሲወስዱን ቆመን አይተናል። አሁን ጊዜው በሀሳብ ልዩነት ስንሞት ቆመን የምናይበት ሳይሆን ተቀምጠን የምንወያይበት ነው።

በብሄራዊ ምክክር መሪነት ተቀምጠን የምንነጋገርባቸው አጀንዳዎቻችን ያንን አዳፋ ታሪካችንን ይቀይሩታል ብዬ በጽኑ አምናለው። ጦርነት የጠፈጠፋትን አገራችንንም እንደ አዲስ ለመፍጠር እድል እናገኛለን። በአለመግባባትና በተለያዩ ልዩነቶች አገራችን ውጥንቅጧ በወጣበት በዚህ ሰዐት ይሄ የምክክር መድረክ እንደ አገር እውቅና አግኝቶ መቋቋሙ አገራችንን ወደ ፊት የሚያራምድ ድንቅ ተግባር ነው ብዬ ማወደስ እሻለው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ችግሮቻችን በምክረ ሀሳብ መፍትሄ አግኝተው ሰላማዊት አገር ስንፈጥር እስከዛሬ ባለመነጋገራችን የከፈልነውን ዋጋ እያሰብን የምንቆጭበት ጊዜ ይመጣል ባይም ነኝ።

ኢትዮጵያዊነት የአንድነት ድር ነው..ሸማኔውም እኔና እናንተ ነን። በአንድ አይነት እጅ፣ በአንድ አይነት እንዝርት ተሹረን ጋቢና ቡሉኮ የሆንን ህዝቦች ነን። በዚህ እንዳይለያይ ሆኖ በተሰናሰለ ማንነት ውስጥ የሌለን ልዩነት እየመዘዙ ማውጣት ለማንም የማይበጅ እኩይ ተግባር ነው። የሚያምርብን እንዴትና መቼ እንደሆነ እናውቀዋለን። የሚያምርብን አንድ ላይ ስንቆም ነው።

የሚያምርብን ኢትዮጵያዊነት ከሰማኒያ መልክና ቀለም ተፈልቅቆ ህያው የሆነ ማንነት እንደሆነ ሲገባን ነው። ያለፉ ታሪኮቻችንን መለስ ብለን ብናጤን ከተለያየንባቸው ይልቅ አንድ የምንሆንባቸው የበዙ እንደሆኑ እንደርስበታለን። ነገር ግን ከዛ ሁሉ እልፍ አንድነታችን ውስጥ ጥቂት ልዩነቶችን እየቆጠርን ለመለያየታችን የምንገፋፋ ነን። እንደ አገር ልዩነት ሊኖረን ይገባል..አይደለም ሰው ከሰው እግር ከእግርም ይጋጫል ትልቁ ጥበብ ግን ልዩነቶቻችን ወደጦርነት ከማምራታቸው በፊት በውይይት መፍታት ነው።

ለውይይትና ለምክክር ክፍት ባልሆነ ፖለቲካ ውስጥ የምትፈጠር ውጤታማ አገር የለችም። ኢትዮጵያን የመሩና እየመሩ ያሉ ብዙዎቹ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ እንድታድግና እንድትለወጥ ጽኑ ፍላጎት ያላቸው ናቸው ነገር ግን ችግሮቻቸውን በውይይት ሲፈቱ አልታዩም። አብዛኛው ችግራችን ከፖለቲካው ተነስቶ ወደማህበረሰቡ የሚፈስ ነው።

ከማህበረሰቡ ተነስቶ ወደፖለቲከኞቻችን የደረሰ ችግር ኢትዮጵያ የላትም። ችግሮቻችን ሁሉ ከፖለቲከኞቻችንና ከፖለቲካው መንጭተው አገርና ህዝብ የሚጎዱ ናቸው። እንደ አገርም ሆነ እንደ ፖለቲከኛ ውይይትን የችግር መፍቻ ቁልፍ አድርገን ልንቀበል

> **ኢትዮጵያዊነት የአንድነት ድር ነው.. ሸማኔውም እኔና እናንተ ነን። በአንድ አይነት እጅ፣ በአንድ አይነት እንዝርት ተሹረን ጋቢና ቡሉኮ የሆንን ህዝቦች ነን**

ይገባል። አንድ አይነት ከሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ወጥተን ዘመኑን የዋጀ የንግግርና የምክክር ስርዐትን ማምጣት ይጠበቅብናል። በችግሮቻችን ላይ ሳንወያይና የጋራ ተግባቦት ሳይኖረን የምንመኘው ህልም ህልም እልም ከመሆን ባለፈ ፋይዳው አይታየኝም።

ሰው የእድሉ ፈጣሪ ነው..ይሄን እውነት ወደአገርና ህዝብ ስናመጣው ህዝብ የአገሩ ፈጣሪ ነው የሚል ይሆናል። እንደ ኢትዮጵያ እድሎቿን በጦርነትና ባለመግባባት ያባከነች አገር አላውቅም። ..ወደጦርነት የወሰዱንን ችግሮቻችንን በሰላማዊ መንገድ ፈተናቸው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ በዚህ ልክ በድህነትና በኋላቀርነት ባልተሰቃየን ነበር እላለሁ።

ድህነትና ኋላቀርነት በተፈጥሮ የሚሰጡ አይደሉም የሰው ልጅ በራሱ መንገድ፣ በራሱ የአኗኗር ዘይቤ የሚሰባቸው ናቸው። ከትላንት እስከዛሬ የተቆራኘናቸውን ድህነትና ነውሮቻችንን በራሳችን መንገድ የፈጠርናቸው እንደሆኑ እማኝ አያሻንም። ከነዚህ ነውሮቻችን ለመውጣት አዲስ አገራዊ አስተሳሰብን መጀመር አለብን..እሱም ከመነጋገርና ችግሮችን በውይይት ከመፍታት የሚጀምሩ መሆን አለበት።

ሰው ሳይወያይና ሳይነጋገር አይደለም ከሌሎች ጋር ከራሱ ጋር እንኳን አብሮ መኖር አይቻለውም። እንደ አገር እድሎቻችንን የሰወርነው ራሳችን ነን። የምንናፍቃት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር የመሳሪያ ድምጽ የማይሰማበት ፖለቲካ ያስፈልገናል። የምንፈልገው አገራዊ ልማትና ብልጽግና እንዲመጣ ውይይትን ያስቀደመ ችግር ፈቺ ምክረ ሀሳብ ያስፈልገናል።

ጀግንነት ያለው በፍቅር ውስጥ ነው። ጀብደኝነት ያለው በይቅርታ ውስጥ ነው። አገራችንን በፍቅርና በይቅርታ ጀግንነት ውስጥ ካልሆነ ካቀረቀረችበት ቀና ልናደርጋት አንችልም።

እየሱስ ጠላቶቹን የረታው በፍቅር ነው። በሰማይም በምድርም ጦር ማዝነብ የሚችል ልዕለ ሀያል ጌትነት እያለው ግን በፍቅር ማሸነፍን መረጠ። አሁን የሚያስፈልገን የይቅርታ ልብ ነው። አሁን የሚያስፈልገን በምክክር የነበሩና ያሉ የሚኖሩም ችግሮቻችንን መፍታት ነው። ጀግና ማለት ስለሀገሩ እያሰበ ስለሀገሩ የኖረ ነው። የጎደለን ነገር ትንሽ ነው፤ ዋጋ እያስከፈለን ያለው ግን ብዙ ነው። ትንሽ ዞር ብለን ምን እንደጎደለን ማየት አለብን። የጎደለን ሰላም ብቻ ነው..የጎደለን ሰላምን በውይይት ማምጣት ነው። ለአገራችን ውለታ ለመዋል አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለን እርሱን የሰላም መንገድ ነው።

አገራዊ የምክክር መድረኩ ለአገራችን ትልቅ ተስፋ ይዞ እንደመጣ አምናለው። በጦርነትና በመገፋፋት የዳበረ ጡንቻችንንም ያለዝብልናል ብዬ ተስፋ አደርጋለው። የእድሎቻችን መፈጠሪያ፣ የተስፋዎቻችን መነቃቂያ እንደሆነ አምነን መቀበል አለብን። እኛ ካልተሳተፍንበት፣ እኛ የመፍትሄው አካል ካልሆንን ግን ብቻውን ምንም ሊያመጣ አይችልም።

መድረኩ በእኛ ለእኛ የቆመ ነው። ከእኛ ውጪ ምንም ኃይል የለውም። ለውይይት ቢቀርቡ የምንላቸውን፣ ትላንትም ይሁን ዛሬ የተፈጠሩ የመገፋፋት ቁርሾዎቻችንን በማንሳትና በመምከር በመወያየትም የጋራ እውነት ላይ የምንደርስበት መድረክ እንጂ ፊት አይቶና አእምሮ አንብቦ በመንካት መፍትሄ የሚሰጠን አይደለም። በነቃ ተሳትፎ ዘላቂ መፍትሄ የምናገኘው ነው። በብሄራዊ ምክክሩ ላይ የምንጠብቀው አካል፣ መፍትሄ እንዲሰጠን የምንተማመነው ኃይል የለም። እኛው ተነጋግረን እኛው የምንግባባበት የእኛው መድረክ ነው።

በሰከነ አእምሮ ማሰብ ከቻልን ብሄራዊ ምክክሩን የለውጥና የመነሳት ምዕራፍ አድርገን ልንወስደው እንችላለን። ችግሮቻችን በምክክር ተፈቱ ማለት አብረው መፍትሄ የሚያገኙ ብዙ ነገሮች አሉን። በአንዲት ትንሽ ችግር ውስጥ የገቡ ብዙ ችግሮች ያሉን ህዝቦች ነን። የዛ ቀዳዳ መደፈን የብዙ ችግሮችን ቀዳዳ ነው የሚደፍንልን። በምክክሩ ትውልድ እንቀርጽበታለን፣ ሰላም እናመ ጣበታለን፣ ያለፈ እኩይ ታሪካችንን እናድስበታለን።

ወደ ፊት ለመሄድ በምናደርገው ጉዞ ላይ ኃይል ሆኖ የሚያራምደን፤ በዚም በዛም የተደቀኑብንን ችግሮች እያጠራን እንድንሄድ በብርቱ የሚያግዘን ይሆናል። ዓለም ላይ አንድ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ማህበረሰቦች የሉም። እንደ መልካችን አመለካከታችንም የዛኑ ያክል የተራራቀ ነው። ግን ደግሞ በልዩነት ውስጥ መግባባት ይቻላል። እኛ ያቃተን በልዩነት ውስጥ መግባባት ነው። ባለመስማማት ውስጥ ያለውን መስማማት እስካሁን አልደረስንበትም። ብዙ ነገሮቻችን ዋጋ ያጡት ለዚህ ነው።

በምክክር ያልተፈታ ችግር በጦርነት አይፈታም። ጦርነት መነሻና መድረሻው ውድመት ነው። ችግሮቻችን ወደ ጦርነት የሚወስዱን ለውይይት የሰፋ ልብና የዳበረ አእምሮ ስለሌለን ነው። የሰላም ምንጫችንን እያወቅን ሰላም ማምጣት አለመቻላችን ሁሌም የሚያሳዝን፤ የሚያስቆጭ ነው። ሰላም ውይይት ውስጥ እንዳለ እናውቃለን..ማወቅ ብቻ አይደለም እናምናለንም። ግን እምነትና ድርጊታችን ለየቅል ነው።

ሰው አርነት የሚወጣው በእውቀት ነው። እውቀታችን ሰላምና ስለሰላም ካልሆነ ስለጦርነት እያሰብን መሽቶ በሚነጋ ፖለቲካችን ውስጥ አገር መፍጠር አንችልም። አገራችንን ከገጠሟት የሰላም ጠንቆች ለመታደግ የሰላም እውቀት ቀዳሚው መርሀችን መሆን አለበት በሰላም እውቀት ተነጋግረን መግባባታችን ለኢትዮጵያ የምንከፍለው የመጨረሻው ውለታችን ነው። ሰላም ወደ ፊት ለመሄድ ወደ ኋላ የምንደረደርበት መስፈንጠሪያችን ነው.. ያልተስፈነጠርነው ሰላምን ሳንይዝ ስለተንደረደርን ነው።

ሰላምን መሰረት ያደረገ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ተግባቦት ያስፈልገናል። የሰላም ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ የገባንን ያክል ምንም ነገር ገብቶን እንደማያውቅ አምናለው። ባለፉት ዓመታት ውስጥ በሰላም እጦት የከፈልናቸው መስዋዕቶች ዛሬም ድረስ እንደሚያሙን ይሄንንም እናውቃለን። ትልቁ ጥያቄ የሚሆነው ትላንታችን እንዳይደገም ዛሬ ላይ ምን እናድርግ የሚለው ነው።

ትላንታችን እንዳይደገም ትላንት ላይ የሌሉ የውይይት መድረኮች ያስፈልጉናል። ትላንታችን እንዳይደገም ልዩነቶችን በእርቅና በምክክር መፍታትን መልመድ ይኖርብናል። እኚህና የመሳሰሉ ገፊ ታሪኮቻችን ናቸው ዛሬ ላይ ይሄን አገራዊ ምክክር እንድናቋቁም እድል የሰጡን። በሰላማዊ መንገድ ሰላማዊ አገር መፍጠር እንደሚቻል ዛሬ ስለገባን በግሌ አዝናለው። ትልቋ አገር..በውብ ቀለም ዓለምን የቀለመች ጦቢያ ዛሬ ላይ የሠላም ሀሳብ አጥታ ሰላም ርቋት ሳይ ይከፋኛል። ከዓለም በፊት በቅላ ከዓለም ኋላ መጽደቋ እንደ ዜጋ ይቆረቁረኛል። ቀላል ነገሮች ናቸው ከባድ ዋጋ እያስከፈሉን ያሉት።

የምኞታችንን ያክል ለአገራችን አንዳች አላደረግንም። ምኞት በተግባር የሚጸድቅ እንጂ በወሬ የሚለማ አይደለም። ጎራዴአችንን ለስየፋ እየሳልን፣ መትረየሳችንን ለመግደል እያነጣጠርን የምንመኘው ሰላም ከኪሳራ ባለፈ ትርፍ አያመጣልንም። ጦራችንን ለበቀል፣ ቀስታችንን ለሞት እያነሳን የምንፈልገው ስልጣኔ ከወሬ ባለፈ መሬት ጠብ አይልም።

ትርፋችንን በምኞታችን መጠንና ብዛት ሳይሆን ለውይይት በከፈትነው ልባችን ልክ ማስላት አለብን። አዲስ ማንነት የአዲስ ህይወት መጀመሪያ ነው። አዲሷን አገራችንን በአዲስ ፖለቲካና በአዲስ ህዝባዊ እርቅ ብንፈልጋት አዋጪ መንገድ ነው። ለዚህ ደግሞ ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን በሚያነሳቸው የህዝብ አጀንዳዎች ላይ አስተያየት በመስጠትና የመፍትሄ አካል በመሆን አንድ ርምጃ መራመድ እንችላለን።

አንድ ቀን ትውልዱ ይጠይቀናል..ዛሬም ድረስ በአባቶቻችን ኢትዮጵያ ስር ነን። የእኛን ኢትዮጵያ መፍጠር አልቻልንም። አንድነትና ወንድማማችነት ያቆማትን የአባቶቻችንን ኢትዮጵያ ሽርፈንና ገምሰን ለማንም እንዳትሆን የፖለቲካና የዘረኝነት ካባ እየደረብንባት ነው። ይሄ ደግሞ ሁላችንንም ከመጉዳት ባለፈ ነጥሎ የሚጎዳው የማህበረሰብ ክፍል የለም። እመኑኝ አንድ ቀን ትውልዱ ይጠይቀናል..ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን።

ለዚህ ትውልድ መልስ ለማዘጋጀት ያልተከፋፈለችና ጦርነትን የሰላም ማምጫ ያላረገች አገር ታስፈልገናለች። ከአባቶቻችን እንደተረከብነው ሁሉ ለልጆቻችን የምናስረክባት በአንድነቷና በነጻነቷ የቆነጀች አገር መስራት ይጠበቅብናል። በታደሰ ፖለቲካና ለእርቅ በቆመ ማህበረሰብ ታጅበን ወደፊት መሄድ ካልቻለ ከነበርንበት የሚያንቀሳቅሰን ምንም ኃይል አይኖርም። በመሸነፍ ውስጥ ማሸነፍን አይነት፣ በመተው ውስጥ ማትረፍን አይነት፣ በይቅርታ ውስጥ መራመድን የመሰለ አዲስ ማንነት ያስፈልገናል። መሄድ ከሚገባን ርቀን ለመሄድ እነዚህ የዘመናዊነት ርሾ በፖለቲካችን ላይ ሊነሰነሱ ግድ ነው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የአርሦ አደሮቹ በመስኖ የመልማት ፍላጎት የወለደው የውሃ መሣቢያ ሞተር ጥያቄ

ስምስም መንግሥቱ

የክረምት ወቅትን ጠብቆ የሚከናወነውን የኢትዮጵያን ግብርና ስራ የሚያውቅ በዚህ ዘመን በበጋ ወቅት አረንጓዴ የለበሰን ማሳ ለዚያም የስንዴ ማሳን አይቶ ላይጠግብ ይችላል።እኔም በአንድ የስራ አጋጣሚ በቅርቡ በወፍ በረር የቃኘሁት የመስኖ ልማት አካባቢ ይህን ስሜት አሳድሮብኛል።አካባቢው ከፊሉ ማሳ በአትክልትና ፍራፍሬ፤ ከፊሉ ደግሞ በበጋ መስኖ ስንዴ ሰብል ተሸፍኗል።ሁሉም አይንን ይስባሉ።

በተለይ በዚህ አቧራ፣ ሀሩር፣ ጸሀይና ሙቀት በተንሰራፋበት የበጋ ወቅት ማሳ በዚህ መልኩ አረንጓዴ ለብሶ ማየት የበጋ ስንዴ መስኖ ልማቱን ፋይዳ በሚገባ ያመልክታል።ከተሰራ በጋውን ሙሉ እህል ማምረት እንደሚቻል በመጠቆምም ትልቅ ተስፋን ያጭራል።

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በዚህ የበጋ ወቅት መመልከት የተለመደ ነው።በቆሎ በመስኖ ወደ ማልማት ከተገባም እንዲሁ ቆይቷል።የስንዴው ግን የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው፤ አግራሞትን በእጅጉ ያጭራል።ልማቱ ለአልሚው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘት፣ ለሸማቹ ደግሞ በተሻለ ዋጋ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ያስችላል።

በአካባቢው ማንኛውም የግብርና ሥራ የሚከናወን ቢሆንም፤ በምርታማነት ግን በአትክልትና ፍራፍሬ፤ ከሰብል ልማት ደግሞ በስንዴና በበቆሎ በስፋት እንደሚታወቅ የአካባቢው አርሶ አደሮች ይናገራሉ።

አካባቢው በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን አዳሚቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ነው።የአካባቢው አርሶ አደሮች አሁን እያከናወኑት ባለው ልማት ደስተኞች ናቸው፤ በቀጣይም የበለጠ ለማልማት ዝግጁ ናቸው። ቀድሞ የሚሰሩበትን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት አጠናክረውታል።በዚህም ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

አርሶ አደር ጀማል በዳሶ ከስንዴና በቆሎ በተጨማሪ አትክልት ያለማሉ።ቀደም ሲል በነበራቸው የግብርና ሥራ ተሞክሮ በክረምት በመኸር ወቅት ስንዴና በቆሎ በበጋው ደግሞ በመስኖ እንደ ቃሪያና ጎመን ያሉትን ያለሙ ነበር።ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን ክረምት ከበጋ ሰብልም ሆነ አትክልት በስፋት ማልማት ውስጥ ገብተዋል፡፡

በሁለተኛው ዓመት የበጋ መስኖ ልማት ስራቸው የሥራ ባህል ተምረውበታል፤ ምርታማነታቸውም ጨምሯል።ውሃ በአካባቢያቸው እያለ አቅጣጫውን የሚመራቸው ወይንም ግንዛቤ የሚሰጣቸው ባለመኖሩ ረጅሙን ወቅት ጠብቆ በማልማት ላይ ተወስነው ለመቆየት ተገደው የነበሩት አርሶ አደሩ፣ ምርታማ ሆነው ኑሮአቸውን መለወጥ ሲችሉ ባለመሥራታቸው ይቆጫሉ።

አሁንም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተፈጠረው እድል በሚገባ ለመጠቀም ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ይናገራሉ።አምና በበጋ መስኖ ስንዴ አልምተው 15 ኩንታል አግኝተዋል።ይህ ለእሳቸው አዲስ ክስተት ነው።የበጋ መስኖ ልማት ብዙ ፋይዳ እንዳለው ነው አርሶ አደሩ የሚናገሩት።ሰብሉ በቂ ውሃ እንደሚያገኝ፣ የግብአት ፍጆታውም አነስተኛ መሆኑን፣ አረምም በዚህ ወቅት እንደሚቀንስ ነው ያብራሩት፡፡

አካባቢው ላይ የዝናብ እጥረት በመኖሩ በመኸሩ ሰብሉ በቂ ዝናብ ስለማያገኝ ምርታማነቱም አነስተኛ ነው የሚሉት አርሶ አደር ጀማል፣ የበጋ መሥኖ ልማት መጀመሩ እርሳቸውን ጨምሮ ለአካባቢው አርሶ አደሮች ጥሩ እድል መፈጠሩን ነው የተናገሩት።ጠንክሮ ከተሰራ ውጤታማ መሆን እንደሚቻልም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመረዳት መቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡

የአካባቢው አርሶ አደር ለመሥኖ ልማት የሚጠቀመው በአቅራቢያው ከሚገኝ ዝዋይ ሐይቅ እንደሆነ የጠቆሙት አርሶ አደር ጀማል ጠቅሰው፣ የተለያየ የስንዴ ዝርያን ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይገልጻሉ።ከእነዚህም መካከል እርሳቸው ‹ቀቀባ›የተባለውን ዝርያ መጠቀማቸውን ይናገራሉ።ይህን ዝርያ ፈጥኖ ስለሚደርስ መርጠውታል።በተያዘው የበጋ ወቅት የዘሩት ስንዴ ለመሰብሰብ እየደረሰ እንደሆነም ገልጸውልኛል፡፡

አርሶ አደር ጀማል ክረምት ከበጋ ማምረት ከጀመሩ ገና ሁለተኛ ዓመታቸው ቢሆንም፣ በኑሮአቸው ላይ ለውጥ አስገኝቶላቸዋል።ይህንንም ‹‹መኪና አልገዛሁም እንጂ ኑሮዬ እየተለወጠ ነው››ሲሉ በጨዋታ መልኩ ነግረውኛል።አርሶ አደሩ የተሻለ መኖሪያቤት መገንባታቸውን፣ ልጆች እያስተማሩ መሆናቸውን፣ በአመጋገብ ሥርአታቸው የመጣው ለውጥ በመግለጽ ህይወታቸው መሻሻሉን ያብራራሉ።

አርሶ አደር ጀማል ከቁጭት ለመውጣት እየሰሩ ናቸው።ለእዚህም ክረምት ከበጋ ጠንክረው መስራት ፈልገዋል፤ በመስኖ ልማት የሚያስፈልጋቸውን የውሃ መሳቢያ ሞተር (ፓምፕ) ማግኘት አለማቻላቸው ግን እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፤ አሁን እየተጠቀሙበት ያለው የውሃ መሳቢያ ሞተር ውሃ የመሳብ አቅሙ አነስተኛ በመሆኑ ከሐይቁ ማሳቸው ድረስ ውሃ ለመሳብ ተቸግረዋል።እየተጠቀሙበት ያለው ሞተር በመንግሥት እገዛ የተገኘ ቢሆንም፣ መንግስት አሁንም የተሻለ ውሃ የመሳብ አቅም ያለው ሞተር በማቅረብ እገዛ እንዲያደርግላቸው ፈልገዋል።ይህም የበለጠ አምራች እንዲሚያደርጋቸው ነው ያመለከቱት።የውሃ መሳቢያ ሞተሩን በራሳቸው ለማሟላት የአቅም ውስንነት እንዳለባቸው ጠቅሰው፣ የበለጠ መሥራት እየፈለጉ ግን በውስን ለማልማት ተገደዋል።በዘር አቅርቦት በኩልም ከመንግሥት በተመጣጣኝ ዋጋ እያገኙ እንደሆነ ተናግረው፣ መንግስት በመስኖ የሚያለማን እያበረታታ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

‹‹አሁን ኑሮ ተወዷል።የሚገዛው ነገር ሁሉ ከአቅም በላይ እየሆነ ነው።እርሻን ማስፋፋትና ተጓዳኝ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል›› የሚሉት አርሶ አደር ጀማል፣ አርቀው በማሰብ መሥራት ያለባቸውንም ከወዲሁ እያቀዱ ነው።ለዚህ ደግሞ ብድር የሚያገኙበት መንገድ ቢመቻችላቸው የመጀመሪያው ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁ ናቸው፡፡

መንግሥት ብድር በማመቻቸት እንዲያበረታታቸው ጠይቀዋል።የመንግሥትን ድጋፍ ብቻ ከመጠበቅ ራስን ለመቻል የሚደረግ ጥረት መኖር የለበትም ወይ? በማለት አርሶ አደር ጀማል ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ‹‹ገበሬ ከዚህ ቀደም ብድርም ሆነ ድጋፍ ጠይቆ አያውቅም።ከተማ ላይ ህንፃ የሚሰራ ነው እየጠየቀ ያለው።መንግሥትም ብድር ሲያመቻች የኖረው ለከተማው ነው።ገበሬው ግን እንዲህ አይነት እድል አልነበረውም።አሁን ላይ ገበሬው ብድር እንዲያገኝ ጥረቶች ቢኖሩም በቂ አይደለም›› ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

አርሶ አደሩ አካባቢው ላይ ለእርሻ የሚውል ትራክተር፣ ማጨጃና መውቂያ ማሽን (ኮባይነር) አቅርቦት እንዳለ ጠቅሰው፣ ውስንነት እንዳለም ተናግረዋል።ከዝዋይ እሳቸው ያሉበት መንደር ድረስ ማሽነሪዎቹን በማስመጣት በአገልግሎቱ ለመጠቀም ዋጋው ከፍተኛ እንደሚሆን ጠቅሰው፣ በዚህ ምክንያት ብቻ አገልግሎቱን እንደማይጠቀሙ ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የሜካናይዜሽን አገልግሎቱ የሚሰጠው እንደ ምርቱ መጠን ነው።ምርቱ ከፍተኛ ከሆነ በኩንታል፣ ምርቱ አነስተኛ ከሆነ ደግሞ በቀርጥ ነው የሚደራደሩት።ሁለቱም ከገበሬው አቅም በላይ ናቸው።በዚህ የተነሳ አብዛኛው አርሶ አደር አገልግሎቱን አይጠቀምም።

በዚህ ረገድ ወረዳው አርሶ አደሩ በዋጋ እንዳይጎዳ ለማድረግ ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር መክሮ ዋጋ እንዲተመን ጥረት እንደሚያደርግ ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩም ጠብቆ እንዲጠቀም ምክር እንደሚሰጥ ገልጸዋል።ይሁን እንጂ በግንዛቤ እጥረት፣ አገልግሎቱን በሚያቀርቡት ግፊትና በደላሎች ተቻኩሎ የመጠቀም ሁኔታ እንዳለ ይናገራሉ፤ ከወረዳው ጋር ያለመናበብ ችግር መኖሩንም ይጠቁማሉ፡፡

በሶስት ሄክታር ማሳቸው ላይ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ስንዴና ገብስ በስፋት እያለሙ እንደሆነ የነገሩኝ ሌላው አርሶ አደር ጌታቸው ዋሾ ናቸው።በ2014 እስከ 2015 ድረስ የመኸር ምርት ዘመን ስለነበራቸው እንቅስቃሴና ስላገኙት ምርት እንዳጫወቱኝ፤ በምርት ዘመኑ አካባቢው ላይ ከፍተኛ የዝናብ እጥረት በመከሰቱ ምክንያት የጠበቁትን ያህል ምርት አላገኙም።የዝናብ እጥረቱ በተለይ በቆሎ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል፤ በእሸትነቱ ከመጠቀም ያለፈ ምርት ማግኘት አልቻሉም።የዝናብ እጥረቱ ባያጋጥምና በወቅቱም አስፈላጊው ግብአት ቀርቦ በደንብ ሰርተው ቢሆን ከሄክታር እስከ 60 ኩንታል ይገኛል የሚል እቅድ ነበራቸው።

አርሶ አደሩ በስንዴና በገብስ ግን የተሻለ ምርት አግኝተዋል።በተለይ ስንዴ በሄክታር እስከ 30 ኩንታል አግኝተዋል።አካባቢው ለጤፍ አመቺ ባይሆንም፣ ለቀለብ የሚሆን ምርት አግኝተውበታል፡፡

አርሶ አደር ጌታቸው፤ እንደ ሌሎች የአካባቢያቸው አርሶአደሮች በበጋ መሥኖ ልማት ውስጥ እንዳልገቡ ይናገራሉ።ዋና ምክንያታቸው የውሃ መሣቢያ ሞተር (ፓምፕ) አለማግኘት ነው።ማሣቸው ውሃ ከሚገኝበት አካባቢ ርቀት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ የውሃ መሣቢያ ሞተር ማግኘት ግድ ነው ይላሉ።አንዳንድ አርሶ አደሮች የውሃ መሳቢያ ሞተር እንዳገኙት ለምን ማግኘት እንዳልቻሉና በውሰትም ቢሆን ለመጠቀም ለምን እንዳልሞከሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ በሁለቱም አማራጭ ማግኘት እንዳልቻሉ ነው የገለጹት።

‹‹አርሶ አደሩ በስፋት በልማቱ ውስጥ እንዲሳተፍ መንግሥት የማነቃቃት ሥራ በመሥራቱ ገበሬው ከወቅታዊ ሥራ ወጥቶ ዓመቱን ሙሉ ለመሥራት ጥረት እያደረገ ይገኛል።ነገር ግን ለመስኖ ልማቱ ግብርናው ሥራ የሚያግዝ አቅርቦት ከሌለ የተፈለገው ውጤት ላይ መድረስ አይቻልም።ለበጋ መሥኖ ልማቱ የውሃ መሣቢያ ሞተር ወሳኝ ቢሆንም፣ በበቂ ሁኔታ እየቀረበ አይደለም›› ሲሉ አርሶ አደር ጌታቸው ያመለክታሉ።የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ወረዳው እያቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአቅርቦት በኩል የፍትሐዊነት ችግር እንዳለም ይጠቁማሉ። በዚህ ላይ የሞተሮቹ ውሃ የመሳብ አቅም አነስተኛ እንደሆነ ነው የገለጹት።እሳቸው በውሃ መሳቢያ ሞተሮች በአቅርቦት በኩል መንግሥት እገዛ ማድረጉን እንዲቀጥል ጠይቀዋል።አቅርቦቱ ብድር ቢመቻች በግላቸው ገዝተው ለመጠቀም ዝግጁ እንደሆኑም ገልጸዋል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን በመጠቀም ረገድም ብዙ ሥራ እንደሚቀር በመጥቀስ የአርሶ አደር ጀማልን ሀሳብ የሚያጠናክር አስተያየት ሰጥተዋል።የሜካናይዜሽን አገልግሎት በዋጋ ውድ መሆንም አርሶ አደሩ የባህላዊውን ዘዴ ወደ መጠቀም እያዘነበለ እንዲሄድ እንደሚያደርገውም ነው የጠቆሙት።አገልግሎቱ ቢሰፋ በውድድር ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

አርሶ አደሮቹ ስለውሃ መሣቢያ ሞተር ያነሱትን እንዲሁም በወረዳው በኩል አርሶ አደሩ የሚፈልገውን በመደገፍና ክትትል በማድረግ በአጠቃላይ እያደረገ ስላለው እንቅስቃሴ በተመለከተ ጥያቄ ያቀረብንላቸው በአዳሚቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ግብርና ጽሕፈትቤት የእንስሳት ሀብትና የዘር ማሻሻያ የሥራ ሂደት አስተባባሪ አቶ ገመቹ ጃምቦ በሰጡት ምላሽ እንዳሉት፤ የአርሶ አደሮቹ ጥያቄ ተገቢነት አለው፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተስፋፋ ከመጣ ወዲህ እና አምርቶ የመለወጥ ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ የውሃ መሣቢያ ሞተር ፍላጎትም እየጨመረ መጥቷል።በተለይ በዚህ ዓመት በግለሰብ፣ በማህበር ተደራጅተው በመስኖ ልማት የተሰማሩ ወጣቶችና ሴት አርሶ አደሮች በስፋት ጥያቄ እያቀረቡ ናቸው።በዚህ ምክንያት ሲሰራበት የቆየው የውሃ መሣቢያ ሞተር አቅርቦት መንገድ የጥያቄ አቅራቢዎችን ፍላጎት ለማሟላት አላስቻለም፡፡

ይህን ሰፊ ፍላጎት ለማሟላት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ገመቹ፣ ወረዳው ቀደም ሲል ያቀረበው የውሃ መሣቢያ ሞተር ጥያቄ በ18ሺ ሄክታር መሬት ላይ ለሚከናወን ልማት እንደሆነ አመልክተዋል።የውሃ መሣቢያ ሞተሮች ከፍተኛ በሆነበት አካባቢ ከፍተኛ መጠን ያለው፣ አነስተኛ ፍላጎት በነበረበት አካባቢ እንደአስፈላጊነቱ ለማቅረብ ጥረት መደረጉን ነው የገለጹት፡፡

በአካባቢው ላይ አሁን ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን ያህል የውሃ መሣቢያ ሞተር ቀርቦ እንደማያውቅ አቶ ገመቹ ጠቅሰው፣ የነበረው ተሞክሮ በኮታ ማቅረብ እንደነበር ገልጸዋል።መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በአቅርቦቱ ላይ ትኩረት መስጠቱን ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያመልክትም ተናግረዋል፡፡

በወረዳው የመኸር ወቅት ስለነበረው የምርት ሁኔታ አቶ ገመቹ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ አካባቢው ላይ የዝናብ እጥረት ተከስቶ እንደነበር እሳቸውም ጠቅሰዋል።ምርቱ የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም በተወሰነ ደረጃም መገኘቱን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ በአሁኑ ጊዜ ውጤታማ እየሆነ ያለው በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ነው።በዚህ እንዲበረታታ እየተደረገ ነው።ከሐይቅ ከሚገኘው ውሃ በተጨማሪ የከርሰ ምድር ውሃም ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ ታስቦበታል።ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር አቅም ስለሚጠይቅ የሌሎች ድጋፍና ትብብር ይጠበቃል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽንም በአካባቢው በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ከአቅራቢዎች ጋር በመወያየት ዋጋ በመወሰን አስፈላጊውን እገዛ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

**«አርሶ አደሩ በስፋት በልማቱ ውስጥ እንዲሳተፍ መንግሥት የማነቃቃት ሥራ በመሥራቱ ገበሬው ከወቅታዊ ሥራ ወጥቶ ዓመቱን ሙሉ ለመሥራት ጥረት እያደረገ ይገኛል። ነገር ግን ለመስኖ ልማቱ ግብርናው ሥራ የሚያግዝ አቅርቦት ከሌለ የተፈለገው ውጤት ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ ለበጋ መሥኖ ልማቱ የውሃ መሣቢያ ሞተር ወሳኝ ቢሆንም፣ በበቂ ሁኔታ እየቀረበ አይደለም»**

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የምርምርና ጥናት እውቅና ለአገር ገጽታ ግንባታ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

**ምርምር የአንድ አገር መሰረታዊ ለውጥ ምሰሶ እንደሆነ ማንም ይረዳዋል፡፡ በዚህም በከፍተኛ ትምህርት፣ ምርምር ተቋማትና በሙያ ማህበራት እንደአገር የተለያዩ ምርምሮች ይሰራሉ፡፡ ሥራውም በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ሆኖም እንደአገር ያለንበት ደረጃ ግን ከዓለም ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካም ጭምር ዝቅተኛ ነው፡፡ በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የምርምር ጆርናሎች ጥራትና ቅቡልነት ብዙ መስራትን የሚጠይቀን ነው፡፡ ታዲያ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ምን እየተከናወነ ነው፤ አሁን ያለው የምርምር ሥራ እንደአገር እንዴት ይታያልና መሰል ጉዳዮችን በማንሳት በትምህርት ሚኒስቴር የምርምር ጉዳዮችና ማህበረሰብ ጉድኝት ዋና ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን ቢኖርን አናግረናል፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር አሁን ባለንበት ወቅት ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ተቋማት ጭምር ተብለው ተለይተዋል። በምን መስፈርት ነው፤ ለምንስ አስፈለገ?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** በነበረን የ70 ዓመት ታሪክ ውስጥ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ከልምዳቸውና ከቆይታቸው አንጻር ተለይተው የሚሰሩበት ሁኔታ ቢኖርም ሳይንሳዊ ዘዴን ተከትሎ ሁሉም ተለይተው እንዲሰሩ የተደረገበት ሁኔታ የለም።በነበራቸው የሥራ ሁኔታና አቅም ልክ በትኩረት መስክ የመለየት እድልም አልነበራቸውም።ሐሮማያን ብንወስድ የግብርና ኮሌጅ ሆኖ ዓመታትን መሻገሩ፤ ኮተቤን ብንወስድም እንዲሁ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሆኖ መቆየቱ ባይካድም ዩኒቨርሲቲዎች እስከ አራተኛው ትውልድ ድረስ በተስፋፉበት ልክ የትኩረት መስክ ተለይቶላቸው እንዲሰሩ አልተደረጉም።ከዚያ ይልቅ ሁሉንም የትምህርት መስክ አካተው እንዲያስተምሩ ነው የተደረጉት።ይህ ደግሞ የሀብት ብክነትን ያመጣል።ሌሎች ተጨማሪ ስራዎች እንዳይከናወኑም ያደርጋል።ስለዚህም ከሦስት ዓመት በፊት ይህ ታሳቢ አድርጎ ወደመሥራቱ ተገብቷል።ዩኒቨርሲቲዎች ዓለምአቀፍ መስፈርትን ተከትለውና አለማ ቀፋዊ ሳይንሳዊ ይዘት ኖሯቸው በትኩረት መስክ እንዲሰሩ ሆኗልም።

በተልዕኮና በትኩረት መስክ ተለይተው እንዲሰሩ ደግሞ የ 10 ዓመቱ ፍኖተ ካርታ ወሳኝ ነበር።አዲሱ የትምህርት ስርዓት ወደ ትግበራ መግባቱም እንዲሁ።በዚህም መስፈርት መሰረት የተለዩ ዩኒቨርሲቲዎች አምስት ሲሆኑ፤ ዓለምአቀፍ ተሞክሮን ያገናዘቡት በምርምር፣ በአፕላይድ፣ በአጠቃላይ (ኮምፕሬንሲቭ) የተከፈሉት እና መንግስት በራሱ በተጨማሪ ትኩረት ይደረግባቸዋል ብሎ የመረጣቸው ሁለት መስኮች ማለትም የሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የሚባሉት ናቸው።ወደፊት እየታየም የሚጨመርና የሚለዩ ዩኒቨርሲቲዎች ይኖራል።

እንዴት ተለዩ ሲባል የምርምሩን ብቻ እንኳን ብናነሳ አንድ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ነው ለማለት ማሟላት ያለበት አነስተኛ መስፈርት አለ።ይህም የመምህራን ወይም የተመራማሪዎች ብዛት፣ የፕሮፌሰሮች ስብጥር ወይም የሰው ኃብት ቁጥሩ፣ ያለው የግብዓት አቅርቦት ሁኔታ፣ ጆርናሎችን የማሳተም ብቃትና መሰል ነገሮች ታይተው ነው።ነገር ግን እንደአገር እነዚህን አነስተኛ መስፈርቶች እንኳን ማሟላት የሚችሉ ዩኒቨርሲቲዎች አልነበሩም።ሆኖም የሉም ብሎ ሥራዎችን ከማቆም በመንግስት በኩል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ቢሰጣቸው ወደመስመሩ ሊገቡ ይችላሉ የተባሉትን መምረጥ ተችሏል።ዩኒቨርሲቲዎቹ ነባሮቹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐዋሳ ፣ ጅማ ፣ መቐሌ ፣ ጎንደር ፣ ባህርዳር ፣ ሐሮማያና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ የምርምር ተቋማት ተብለው የተለዩት ዩኒቨርሲቲዎች ምርምር ብቻ ነው የሚሰሩት ወይስ ዩኒቨርሲቲዎች ከዚህ ቀደም የተሰጣቸውን ሦስቱን ዋና ዋና ተልዕኮዎችንም ይፈጽማሉ ?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** እርሱ ግድ ነው።ምክንያቱም አንድ ዩኒቨርሲቲ ምሉዕ እንዲሆን ዩኒቨርሳል የሆነ ሥራ መስራት አለበት። ለዚህ ደግሞ መማር ማስተማር፣ ምርምርና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ማከናወን ወሳኝ ናቸው።ይህንን መስራት ካልተቻለ ምንም መተግበር አይቻልም።ስለሆነም የማይቀሩ ጉዳዮች ናቸው።ይሁን እንጂ ከእነዚህ ውስጥ ተለይቶ የተሰጠውን ሥራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማከናወን ይጠበቅበታል።ማለትም የምርምር ተቋማቱ ምርምር መለያቸው ነውና እርሱን ተኮር ሥራዎች በስፋት ያከናውናሉ። በድህረ ምረቃ ላይ ያተኮረ ምርምር በዋናነት ይሰራሉ ምርምር ደግሞ ሁለቱን ዋና ዋና ተልዕኮዎችን ካልያዘ ስኬታማ ሊሆን አይችልም።

የምርምር ተቋማት የሚሰሩት ምርምር የአገሪቱን አጀንዳ የሚያስፈጽም ነው።የመንግስትን ፖሊሲ አቅጣጫዎችንና ምክረ ሀሳቦችን ያመጣል፤ ወደ መሬት እንዲወርድና በአግባቡ እንዲታይም ያደርጋል። ስለዚህም በእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ሥራዎች ልዩ ትኩረት ያገኛሉ ማለት እንጂ ዋና ተልኮውን አይተገብሩም ማለት እንዳልሆነ መወሰድ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- በየዓመቱ እንደሀገር ምን ያህል ጆርናሎች ይታተማሉ፤ ችግር ፈቺነታቸውስ በምን ይለካል?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** በዓመት ብቻ ሳይሆን በወራትም ጭምር የሚቋቋሙ አዳዲስ ጆርናሎች አሉ።ምክንያቱም አሁን በዚህ ጊዜ ስንነጋገር በምርምር ተቋማት፣ በዩኒቨርሲቲዎች አዳዲስ የሚቋቋሙ ይኖራሉ።ስለዚህም መናገር የሚቻለው እስካሁን ባለው መረጃ ነው።እናም እስካሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ከ 185 እስከ 200 የሚደርሱ ጆርናሎች አሉ።እንዴት በቁጥር ተለይተው ታወቁ ከተባለ ደግሞ የምርምር ጆርናሎችን ማነው የሚያስተዳድረው፤ ማነው የሚያቋቁመው የሚለውን መመለስ ያስፈልጋል።ከዚህ አንጻርም ይህንን የሚያደርጉ ተቋማት በዋናነት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና የሙያ ማህበራት ናቸው። ስለዚህም እነርሱ በሚያመጧቸው መረጃዎች ይታወቃል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ማሳያ ችግር የፈታ የምር ምር ሥራ በየትኛው ተቋም ተሰራ፤ ያስገኘው ውጤትስ ምንድን ነበር ?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** እዚህ ላይ ልብ ሊባሉ ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ምርምር ችግር ፈቺ ብቻ ነው ወይ የሚለው ነው።ምርምር አንድ ተመራማሪ ሳይንሱን አውቆ በምርምር የተለዩ ዘርፎችን ወዲያውኑ ማህበረሰብን የሚጠቀምበት ወይም ደግሞ ቆይቶ በሂደት ግኝት በማግኘት፤ ንድፈ ሀሳቦችን በማምጣት፤ ግምታዊ ትንታኔዎችን በመስጠት በሂደት ማህበረሰቡ እንዲጠቀምበት የሚያደርግ ነው።ስለዚህም ምርምር በይዘቱ መሰረታዊ አለያም ችግር ፈቺ (አፕላይድ)ና በእነዚህ በሁለቱ መካከል የሚሰራ ሊሆን ይችላል።እናም ምርምሮች በሙሉ ችግር ፈቺ ናቸው ተብሎ መወሰድ የለበትም።ሀሳብ አመላካች፣ መረጃ ሰጪ፤ እውቀት አሻጋሪና መሰል ጉዳዮችን በማመላከትም የሚተገበሩ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲዎች እንደ አገር፤ እንደ አፍሪካ በምርምር ሥራቸው የቱ ጋር ናቸው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ኢትዮጵያውያን ከአፍሪካ በሕዝብ ብዛታችን ከናይጀሪያ ቀጥለን እንገኛለን።በዚህም ችግሮቻችን ብዙ ናቸው። እናም ምርምሮቻችን በሙሉ ችግር ፈቺ ብቻ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።ምርምር ግን ከችግር ፈቺነቱ ባሻገር በሳይንስና በንድፈ ሀሳብ አዲስ እውቀት፣ አዲስ ፈጠራ፣ አዲስ እይታና አዲስ መረጃ ማምጣትና መስጠት ነበር አላማው።ይህ ግን እንደ አገራችን በስፋት ሲሰራበት አይታይም። በዚያው ልክ ኢትዮጵያ በምርምር ስራ የሚሳተፉ በርካታ ምሁራንና ተመራማሪዎች፤ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎችና ከፍተኛ ተቋማት አሏት።በሀብት ደረጃም እንዲሁ በቂ ሀብት ይገኝባታል።ሆኖም ከአፍሪካውያን ጋር ስትነጻጸር እጅግ ዝቅተኛ የምርምር ሥራን ነው ለዓለም የምታበረክተው።

ደረጃችን የት ነው የሚለውን ስንመልሰው እንዳለን የከፍተኛ ተቋማት ብዛት፤ እንዳለን የምርምር ተቋም ብዛት መስራት ያለብንን ያህል አልሰራንም።ለምሳሌ 57 የሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች አሉን።አምስቱ የግል ዩኒቨርሲቲዎች ሲሆኑ፤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች ናቸው።ከ250 በላይ ኮሌጆች አሉን።ዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ከተባለ ደግሞ ሦስቱን ተልዕኮዎች ይዞ ማስቀጠል ግድ ነው።በግል ተቋማት ላይ ግን ይህ ይደረጋል ወይ የሚለው መልሱ የሚታይ ነው። ትኩረታቸው ትምህርትና ማስተማር ላይ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል።ከዲፕሎማ እስከ ሦስተኛ ድግሪ ድረስ ትምህርት እየሰጡ ቢቀጥሉም ምርምር ላይ ግን ሲሰሩ አይታይም።ይህና መሰል ችግሮች ከአፍሪካ ጋር ስንነጻጸር ብዙ ይቀረናል ።

ለአብነት በምርምር ጆርናሎችን ብቻ ብናነሳ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ላይ እውቅና ያገኘችባቸው እስከ 2022 ድረስ ባለው መረጃ አራት ብቻ ናቸው።በህዝብ ብዛትም ሆነ በዩኒቨርሲቲዎች ብዛት የምታንሰን ደቡብ አፍሪካ ግን ከ125 በላይ በሆኑ ጆርናሎች አለማቀፋዊ እውቅናን አግኝታለች።የሳይንቲፊክ መስፈርቱን አሟልተውም አገርን በመወከል ሌሎች እንዲጠቀሙባቸው ሆነዋል።ለዚህ ያበቃቸው ደግሞ የምርምር አሰራር ምህዳራቸው ነው።ስለዚህም እንደአገር ዩኒቨርሲቲዎቻችን እውቅና ከማግኘቱ አንጻር ያሉበት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነው።ብዙ ክፍተቶች አሉባቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት ከማን ምን ይጠበቃል?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ሥራው ከግለሰብ ይጀምራል። ተመራማሪው በዓለም ጭምር በሥራው ታውቆ አገሩን ለማስጠራትና ሕዝቡን ለመጥቀም ብሎ መስራት ይኖርበታል። ከዚያ ደግሞ ተቋማት የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው። ማለትም ዩኒቨርሲቲዎች፣ እነርሱን የሚያስተዳድረው ትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም መንግስት የየራሳቸውን ድርሻ ወስደው መስራት ይገባቸዋል። በተለይ እንደመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን በማስፋቱ ደረጃ ብዙ እንደሰራ ሁሉ የምርምር ጥራት ላይም ስርዓቶችን አስፍቶ መስራት ይኖርበታል። ስለዚህም ተመራማሪዎችን ሊያሰራ የሚችል የአሰራር ስርዓት መፍጠር እንደአገር እጅግ ያስፈልጋል።

ደቡብ አፍሪካ ከአፍሪካ በምርምር የላቀች የሆነችው በመንግስት ደረጃ ምርምር እንዴት መመራት አለበት ተብሎ ብሔራዊ ተቋም በማቋቋማቸው ነው።ተቋሙ የሚተዳደረው ከመንግስት በሚሰጠው በጀት ብቻ ሳይሆን ከምርምሮች በሚያገኘው ገንዘብ ነው።የዓለምን የምርምር የሳይንስ አካሄድ እያየ ከመንግስት በጀት በላይ እየተወዳደረ የራሱን ገቢ ያመነጫል።ሩቅ ሳንሄድ ዩጋንዳ የዚህ አይነት አሰራር አላት። በኢትዮጵያ ግን ይህ ሁኔታ አልተፈጠረም። የምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎችን የሚያስተባብር ብሔራዊ የምርምር ተቋም የለም። እስካሁን ባለው መረጃ ምርምሮች የሚመሩት በኮሚቴ ነው።ምርምር ደግሞ በኮሚቴ አይመራም።ምክንያቱም የምርምር ተቋማት በስብጥር ነው ያሉት።እነዚህን ለማሰባሰብ የግድ አገራዊ ተቋም ያስፈልጋል።

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ ምርምር ላይ ትኩረቱን የሚያደርግ ምክር ቤት አለ።ነገር ግን እርሱ ሁሉንም አሰባስቦ የሚሰራ አገራዊ ተቋም አይደለም።እናም ይህንን ተረድቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ውስን ሀብት ለምርምር በጀት ከማዋል ይልቅ ምርምሮች በራሳቸው የገቢ ምንጭ እንዲፈጥሩ ማድረግ የመንግስት ሥራ ሊሆን ይገባል።ይህ መሆኑ ያለውን ጠቀሜታ ለማሳየት አንድ ምሳሌ ብቻ ልጥቀስ።በአውሮፓ ህብረት ስር ያለው ሆራይዞን 100 ቢሊዮን ዶላር ለአፍሪካ አገራት ለምርምር ሥራ ይሰጣል።ሆኖም የእኛ ተደራሽነት በጣም አናሳ በመሆኑ አገራዊ ተቋምም ስለሌለን ተበታትኖ ይቀራል።ስለሆነም እንደነዚህ አይነት በጀቶችን መጠቀም ካስፈለገ ብሔራዊ የምርምር ተቋም እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል።

አዲሱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲም ይህንን እንዲያይ በተደጋጋሚ ተነጋግረንበታል።ተቋሙ ደግሞ የሚመራውም በተመራማሪው እንጂ በፖለቲከኛ አይደለም።ከዚያ ባሻገር የአገር ውስጥ ጆርናሎችን ቁጥር ማብዛት ላይ ሳይሆን ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማስቻል ላይ መስራት ይገባል።ለዚህም የፍተሻና የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት ይገባልና ትምህርት ሚኒስቴር ከሦስት ዓመት በፊት ጀምሮታል። በዚህም በመጀመሪያው ዙር ጥሪ ተላልፎ ወደ 16 ጆርናሎች እውቅና እንዲያገኙ ሆነዋል። በሁለተኛው ዙርም እንዲሁ 23 ጆርናሎች እውቅና አግኝተዋል።በድምሩ 39 ጆርናሎች እውቅና ተሰጥቷቸዋል።እንደሚባለው ምንም አልተሰራም የሚያስብለን ላይ ግን አይደለንም። በምስራቅ አፍሪካ እንኳን ሲታይ የጆርናል ህትመታችን ደረጃ ጨምሯል። አሁንም ይህንን ሁኔታ ከፍ ለማድረግ በብሔራዊ ደረጃ ተሰርቷል የሚለውን ጆርናል ለማሳየት ከመጋቢት 28 እስከ 30 አገርአቀፍ የምርምር አውደጥናት በሳይንስ ሙዚዬም ይካሄዳል።አላማውም ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ምርምር ተሰራ፤ እነማን ሰሩት፣ እንዴት እናሻሽለው፣ ክፍተቶቹ ምን ይመስላሉና መሰል ጉዳዮችን ማመላከት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በየዓመቱ እውቅና ይሰጣል። እውቅናው ደግሞ ምርምር ተኮር ነው።ስለመሆኑ ምን አይነት ውጤት ስለአመጡ ነው በዚህ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ የሆነው፤ መለያውስ ምን ነበር ?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** መለያው የህግ ማዕቀፍ ነው። ጥራታቸው እንዴት ይፈተሻል የሚለውን በዓለምአቀፍ መስፈርት (ስታንዳርድ) መሰረት ታይቷል።አንድ ጆርናል ለመምረጥ ቢያንስ አነስተኛ መስፈርቱን ማሟላት ይኖርበታል። ለምሳሌ ኤዲቶሪያል ይዘቱ ምን ይመስላል፣ የምርምር ልምዱስ፣ የምርምር አርታኢው እንዲሁም በትንሹ ሦስት ዓመት አገልግሏል ወይ የሚሉት ይገመገማሉ።ውስጡ ያለው ቴክኒካል ይዘትም (ኮንቴንትም) ይመረመራል።ከዚያ እውቅናውን ይሰጠዋል። እስካሁንም ለ39 ጆርናሎች እውቅና ተሰጥቷል።ይህ ማለት ግን ምንም እንኳን አለማቀፋዊ የሳይንስ መስፈርትን ይዘን ብንለየውም በአገር ውስጥ ያለውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ብቻ ነው እኛ ልናረጋግጥ የምንችለው።

በአለማቀፋዊው ደረጃ ምን እንደሚባሉ አይታወቅም። ሳይንቲፊክ የሆነ ልዩነት የመፍጠሪያ ዘዴም ያለው በመሆኑ ከአፍሪካ እንኳን ተወዳድረው የተለዩ አይደሉም።ይህ እውቅና በአለማቀፉ ደረጃ ውስጥ ገብተው እንዲወዳደሩ እድል የሚሰጥ ብቻ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የእውቅና መርሃግብር ምንን ታሳቢ አድርጎ የሚሰጥ ነው?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** እውቅናው አንድ የአገር ገጽታ መገንቢያና ማሻሻያ ነው።ክፍተት መሙያና ከፍታን ማሳያም ነው። በሌላ በኩል እውቅና የምርምር ቱሩፋቶችን ማግኛና ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነትን መጨመሪያ ነው።አሁን የተለያዩ ጆርናሎችን በጥራታቸው እየጨመርን ሄድን ማለት አለምላይ እያስቀመጥን የምንመጣው ሥራ ይሰፋል ማለት ነው።ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋይፖ( ወርከ ኢንተሌክችዋል ፕሮፐርቲ) የሚባል አርጋናይዜሽን ኢትዮጵያ በምርምርና ጥናት የት ላይ እንዳለች ሲያስቀምጥ ሁልጊዜ መጨረሻ ያደርጋታል።እናም ይህንን ለመቀየር እንደነዚህ አይነት እውቅናዎች ግድ አስፈላጊ ናቸው።በዓለም አቀፍ ደረጃ ጆርናሎችን የማወዳደርና የማለፍን እድልን ይጨምራልና።

የተመራማሪዎችን ተነሳሽነትም ይጨምራል።የምርምር ባህላችንም ይዳብራል።ኢትዮጵያ በምርምር ላይ ያላት ተሞክሮም ይሰፋል።የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫንም መልካም ተጽዕኖዎችን በመፍጠር ሊያስቀይር ይችላል። ምርምርና ልማት ላይ ትኩረት መስጠት የአንድ አገር የሰለጠነ አካሄድን መምራት እንደሆነ ይታወቃልና አገር በዚህ እንድትመራ ያደርጋታል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪ እናመሰግናለን**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# «በእስራኤል አገር ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት እንፈልጋለን»

**በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር**
**አምባሳደር አለልኝ አድማሱ**

ሞገስ ጸጋዬ

**እስራኤል እንደ አገር ከተመሰረተችበት እ.ኤ.አ ከ1948 ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ሁለንተናዊ ግንኙነት ጠንካራ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በግብርና፣ በጸጥታ፣ በቴክኖሎጂ እና በባህል ዘርፎች የሚደረጉ ግንኙነቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህንኑ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ከእስራኤል በኩል ፍላጎቱ መኖሩም ይታወቃል፡፡ በዚህ በሁለቱ አገራት ግንኙነት ዙሪያ በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር ከሆኑት ከአምባሳደር አለልኝ አድማሱ ጋር አዲስ ዘመን ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያና በእስራኤል መካከል ቀደም ባለው ጊዜ የነበረውና አሁን ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** የኢትዮጵያና የእስራኤል መንግስት ግንኙነት በታሪክ እንደሚታወቀው አንድ ሺ ዓመት ያስቆጠረ ነው።ቀደም ባለው ጊዜያት በሁለቱ አገራት መካከል ጠንካራ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና እና የንግድ ልውውጥ ይደረግ ነበር።ይህ አሁንም እንደቀጠለ ነው።እውነታውን የሚያጠናክሩ መረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እና በተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ አይሁዶች ከእስራኤል አገር የተበተኑት ሁለተኛው ቤተመቅደስ ሲፈርስ ነው፤ በዚህ ወቅት አይሁዶች በመላ ዓለም ተበትነዋል።ለአብነትም የሄዱት ወደ ኤዥያ፣ አውሮፓ፣ አረብ አገራትና ወደ አፍሪካ ነው።በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እስራኤል አፍሪካን፣ ኤዥያንና የአውሮፓን አገራት ታዋስናለች።ወደ አፍሪካ ሲበተኑ ደግሞ በግብጽ አድርገው ወደ ቱኒዝያ፣ ሞሮኮ፣ ሊቢያና ኢትዮጵያ ገብተዋል፡፡

እኛ የኢትዮጵያ አይሁዶች በኢትዮጵያ ሁለት ሺ ዘመን የኖርን ነን።አባቶቻችንና ቅደመ አያቶቻችን የአይሁድ እምነትን ጠብቀው ከኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጋር አብረው ተዛምደው የኖሩ ናቸው።የኢትዮጵያ መነኮሳት ከሺ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እየሩሳሌም ይኖራሉ።ኢትዮጵያ በእስራኤል መሬት፣ ድንበርና ቤተክርስቲያን አላት።ወደ እየሩሳሌም ለተለያዩ በዓላት የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ብዙ ናቸው፤ ይህም የሁለቱን አገራት ህዝቦች ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

ጥምቀት በመጣ ቁጥር በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ እስራኤል በመሄድ በዮርዳኖስ ውሃ ይጠመቃሉ። በእስራኤል የኢትዮጵያ ንብረት በሆነው ጎሎጎታና በዴር ሱልጣን ቦታ ጸልየው ይመለሳሉ።እንዲህ አይነቱ ግንኙነት በሌላ አገር የሌለና ጠንካራ የሚባል ግንኙነት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሁለቱ አገራት መካከል የሚካሄዱ የተለያዩ የጋራ ፕሮጀክት አሉ።ለአብነትም የሰው ማጓጓዣ አውሮፕላንን ወደ ካርጎ (የእቃ ማመላለሻ) የመቀየር ስራ እየተሰራ ነው።በዚህ ዘርፍ እውቀት ያላቸው ቤተ እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ይሰራሉ።ይህ የሁለቱን አገር ግንኙነትም በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በህክምናው ዘርፍም በርካታ ዶክተሮችና አንደኛ ደረጃ ነርሶች አሉ፤ እነርሱም ያላቸውን እውቀት በመያዝ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እገዛ ያደርጋሉ።ከዚህ ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያዊ ነው።በኢትዮጵያ ካሉ የተለያዩ ሆስፒታሎች ጋር በመሆን በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች በመዘዋወር ህክምና ይሰጣሉ።እንዲሁም በሌላ ዙር ቤተ እስራኤሎች ሌሎች እስራኤሎችን በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በህክምናው በኩል ብዙ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

በጸጥታው ዘርፍም ከኢትዮጵያ የሄዱ ወጣቶች በጸጥታው ዘርፍ ሰልጥነው ከፍተኛ ባለሙያ ደረጃ በመድረስ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በትብብር ስራዎች እየተሰሩ ነው።የእስራኤል ሕብረተሰብ ኢትዮጵያን በጣም ይወዳል፤ እንኳን ኢትዮጵያ ተወልደን እትብታችን ኢትዮጵያ የተቀበረው ይቅርና ልጆቻችን


ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

ኢትዮጵያን ይወዳሉ፤ ወደ ኢትዮጵያም የመምጣት ፍላጎት አላቸው።

በዚህ ዓመት ‹ጎንደርን ማክበር በጎንደር› በሚለው አብሮ ጥምቀትን ለማክበርና ለመሳተፍ ከሰባት ሺ በላይ እስራኤላውያንና የኢትዮጵያ አይሁዶች መጥተዋል።በዚህ ሂደት በርካታ ገንዘብ ይዘው ይመጣሉ፤ በቆይታቸውም ለኢትዮጵያ የቱሪዝም እድገት ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ።ወደ አውሮፓና ኤዥያ ከመሄድ ይልቅ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ይወዳሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የእርስ በርስ ግጭት ወቅት በርካታ ተፈናቃዮች አሉ።በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ አይሁዶች ድጋፎችን አሰባስበው ልከዋል። በእስራኤል በርካታ ዓመት የኖርን ባለመሆናችን ብዙ ሀብት የለንም፤ ነገር ግን ህዝቡ በሚችለው ልክ እርዳታ ያደርጋል።ገንዘብ በማዋጣትና በጦርነት ሳቢያ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመርዳት ብዙ ሺ የሚሆን ዶላሮችን በማሰባሰብ ለኢትዮጵያ መንግስት ልከናል።

ለፈረሱ ጤና ጣቢያዎችና ትምህርት ቤቶች ድጋፍ የሚያደርጉት ብዙዎች ናቸው።እንዲሁም ለመገልገያ የሚውሉ ቁሶችን በመሰብሰብ ወደ ኢትዮጵያ ይልካሉ።በእርዳታ የመጣውን ድጋፍ ከጉምሩክ ለማሳለፍና ለመንግስት ለመስጠት ብዙ የአሰራር ችግሮች አሉ።ይህን መንግስት ማየትና መፈተሽ አለበት።

ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ማከማቻ (ስቶር) ውስጥ ይቀመጣል፤ ለመንግስት እስኪተላለፍ ድረስ የተቀመጠበትን ገንዘብ ክፈሉ ይባላል።ለድጋፍ የሚመጣ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ድርጅት ይሁን መንግስት አጋር መሆን አለባቸው።በዚህ መንገድ በድጋሚ ለመስራት ችግር ይሆናል።የኢትዮጵያ አይሁዶች ብዙ ጥረት እያደረጉ ነው።

እኔም የተወለድኩበት አገር በመሆኑ ለመስራት ትልቅ ፍላጎት አለኝ፤ በኢትዮጵያ የውጭ ጣልቃገብነት ሲኖርና ኢትዮጵያን ሲከፋት የኢትዮጵያንና የእስራኤልን ሰንደቅ ዓላማ ይዘን ‹‹ኢትዮጵያ አትነካም›› እያልን ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣለን።ይህን የምናደርገው ነጮችን

> **በኢትዮጵያ የውጭ ጣልቃገብነት ሲኖርና ኢትዮጵያን ሲከፋት የኢትዮጵያንና የእስራኤልን ሰንደቅ ዓላማ ይዘን «ኢትዮጵያ አትነካም» እያልን ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣለን፡፡ ይህን የምናደርገው ነጮችን ሁሉ ይዘን ነው**

ሁሉ ይዘን ነው።

በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ አይሁዶች ብዙ ድጋፎችን አድርገዋል፤ የአባይን ግድብ በተመለከተ ቦንድ ገዝተናል።ከራሴ ጀምሮ ብዙ ስራዎችን ሰርተናል።ሕብረተሰቡም በእስራኤል የኢትዮጵያን ባህል በተለይ አበላሉንና ዘፈኑን ያስተዋውቃል፡፡

በዚህም የኢትዮጵያን ህዝብ እያስተዋወቅን የእስራኤልና የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲጠነከር በማድረግ ላይ ነን።የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማጠናከር የኢትዮጵያ ወጣቶች የእግር ኳስ ቡድን ከእስራኤል አቻው ጋር ተጫውቶ መጥቷል።ወደፊትም ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የነበራችሁ ቤተ እስራኤላውያን በእስራኤል ያጋጠማችሁ ትልቁ ተግዳሮት ምን ነበር?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል የሄዱ በርካታ ቤተ እስራኤላውያን የገጠር ሰዎች ናቸው።እኔም ወደ እስራኤል የገባሁት ከጎንደር አዘዞ ከገጠራማው ክፍል በመነሳት ነው።ኃይማኖቱን ለመጠበቅ በማሰብ በርካታ ቤተ እስራኤላውያን የሚኖሩት በገጠር ነበር።በከተማ በርካታ ሰዎች ስላሉ የመደባለቅ ነገር ይኖራል ተብሎ ይፈራ ስለነበር በርካታ እስራኤላውያን ከከተማ ይልቅ በገጠር መኖርን ይመርጡ ነበር።ከእስልምና እና ከክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች ጋር በፍቅርና በአንድነትም ይኖሩ ነበር፡፡

ቤተ እስራኤላውያን ወደ እስራኤል አገር ሲሄዱ ያልተማሩ ነበር ማለት ይቻላል።ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ብዙ ነበሩ።ነገር ግን ለብዙ ሺ ዓመታት ኃይማኖቱን ጠብቀው የኖሩ ናቸው።እስራኤል በእ.ኤ.አ በ1948 ነጻነቷ ከእንግሊዝ ስታገኝ አይሁዳውያን ከተለያዩ አህጉሮች አገራቸውን ለመገንባት ሲመለሱ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ቤተ እስራኤላውያንም ወደ እስራኤል ተመልሰናል፡፡

ከኢትዮጵያ የሄድን ቤተ እሰራኤላውያን ከሰለጠነ አገር ከመጡ እስራኤላውያን ጋር ለመወዳደር ችግር ነበር።በእውቀትና በስልጣኔ ትንሽ ሊዛመዱ የሚችሉ ከአረብ አገራት ከመጡ እስራኤላውያን ጋር ነበር።ነገር ግን ከዘመኑ ጋር ለመሄድና ከሌላ አህጉር ከመጡ እስራኤላውያን ጋር እኩል ለመሆን ብዙ ጥረት እናደርግ ነበር።በስልጣኔ እኩል ለመሆን ብዙ ለፍተናል።በአሁኑ ጊዜ የቤተ እስራኤላውያን እውቀትና ስልጣኔ ከማንኛውም ጋር የማይተናነስ ደረጃ ላይ ደርሷል።

ከኢትዮጵያ አርሶ አደር ሆኖ የሄደው አሁን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተከታትሎ ትልቅ ደረጃ መድረስ ችሏል።በውትድርና ብዙ ኦፊሰሮች አሉ፤ ዶክተሮች በሀይቴክ ውስጥና በዲፕሎማሲው ዘርፍ ብዙ ቤተ እስራኤላውያን አሉ።በርካታ ወጣቶች በዲፕሎማሲው ዘርፍ ውስጥ ይገኛሉ። በተለያዩ የስራ ዘርፎች በርትተው እየሰሩ ነው። አሁን ያለንበትን ደረጃ ከተነሳንበት ደረጃ ጋር ስናወዳድረው ሰማይና መሬት ነው።የሁለቱ አገር ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆንም በሙያችን እገዛዎችን እያደረግን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሁለቱ አገራት መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዴት ይገመገማል?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** አሁናዊ የኢትዮጵያንና የእስራኤልን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ስንመለከት ወደ ኋላ መሄድን ይጠይቃል።እስራኤል እንደ አገር ከተቋቋመች እ.ኤ.አ በ1948 ከአራት ዓመት በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጀምራለች።እስራኤል ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ችግሮች ይገጥሟት ነበር።ኢትዮጵያም ከእስራኤል ጋር ባላት ጠንካራ ግንኙነት የተነሳ ብዙ ጫና ይደርስባታል።የሁለቱ አገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሊቋረጥ ይገባል እያሉ ጫና የሚያደርጉ ብዙ አገሮች ነበሩ። ለተወሰነ ጊዜም ተቋርጦ ነበር ።

በደርግ ጊዜ ግንኙነቱ ወደ ነበረበት ቢመለስም የደርግ ስርአት ሲከተል ከነበረው የኮሚኒስት ስርአት የተነሳ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ተቋርጦ ቆይቶ እ.ኤ.ሌ ከ1991 በኋላ ተመልሶ ታድሷል፤ አሁንም ጠንካራ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡

በርግጥ በወቅቱ በመንግስት ደረጃ ያለው ዲፕሎማሲ ቢቋረጥም ጠንካራ የሆነ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ስለነበር ግንኙነቱ ጠንካራ እንደሆነ መዝለቅ ችሏል።በመንግስት ደረጃ የነበረው ግንኙነት መውረድና መውጣት ሲያጋጥመው የህዝቡ ግንኙነት ሁልጊዜም ጠንካራ ነበር።በዚህም ጥሩ የሆነ ግንኙነት አለ፤ ይህ አሁንም ቢሆን እየተጠናከረና እተስፋፋ ነው፡፡

# ወቅታዊ



**በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ መንግስትና የህዝቡ ትኩረት ከልማት ይልቅ ጦርነቱን ማርገብ ነበር፡፡ ይህን ከባድ ፈተና አልፎ ወደ ልማቱ እየተገባ ነው፡፡ አሁን ጥሩ ጀማሮ አለ፤ በተለይ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት በጣም የሚደነቅ ነው**

በእስራኤልና በኢትዮጵያ መካከል ጥሩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ስለመኖሩ ባለፈው ጊዜ የሁለቱ አገራት ፕሬዚዳንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሮች ተገናኝተው መወያየታቸው አንዱ ማሳያ ነው።በኢትዮጵያ የእስራኤል ኤምባሲ ከመንግስት ጋር ጥሩ ግንኙነት አለው፤ በተለያዩ ጊዜ ሚኒስትሮችን እያገኘን እንነጋገራለን፤ በጋራ ስራዎችንም እየሰራን ነው።

የእስራኤል ባለሀብቶችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በማድረግ ብዙዎች በኢትዮጵያ እያለሙ ይገኛሉ።በህክምና፣ በግብርና እና በመሳሰሉት ዘርፎች መጥተው ስራዎችን ለመስራትና ድጋፍ ለማድረግ እቅዶች ቢኖሩም አልፎ አልፎ በኢትዮጵያ የሚፈጠሩ ግጭቶች ለስራ እንቅፋት እየፈጠሩ ነው።የሚመጡ ድርጅቶች መስራትና ማትረፍ ቢፈልጉም፤ ያላቸውን መዋዕለነዋይ ማፍሰስ ይፈራሉ፡፡

እስራኤል እንደ አገር እንዳትኖር ብዙ ችግሮች አሉባት፤ እስራኤል ግን ሰላምን የምትፈልግ አገር ናት።ይህን ብዙ የአረብ አገራት በመረዳት ከጉዳቱ ጥቅሙ እየገባቸው አብሮ ለመስራት ከስምምነት እየደረሱ ነው።በርካታ የአረብ አገራት ከእስራኤል ጋር ስምምነት እያደረጉ ነው፤ በዚህም ግልጽና ግልጽ ያልሆነ ግንኙነት አሉ፡፡

እስራኤል ልክ እንደ ኢትዮጵያ በውሸት ስለምትከሰስ በዲፕሎማሲ መስክ የኢትዮጵያን ድጋፍ ትፈልጋለች።ጦርነቱ አልሆንላቸው ሲል የዲፕሎማሲ ጦርነት ጀምረውብናል፤ የእስራኤል ወታደር እየተመታ ጉዳት የማያደርስ ነው።በእስራኤል ላይ በርካታ ሮኬቶች ሲወነጨፉባት እየዋለ ለፍልስጥኤም የሚሄደውን ውሃ አትቆርጥም።

ይሁን እንጂ በዲፕሎማሲው ረገድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትከሰሳለች።በዚህ ወቅት ከኢትዮጵያ እንደ ወዳጅ አገር ድጋፍ እንዲሰጠን እንሻለን።ኢትዮጵያን ለመጉዳት በርካታ የውሸት ዜናዎች እንደሚሰራጩት ሁሉ በእስራኤልም ላይ እንዲሁ ይሆናል።ይህን በተመለከተ በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እስራኤል በዘመናዊ ግብርና፣ ሰው ሰራሽ ዝናብ በማዝነብ፣ በታዳሽ ኃይል፣ እና በመከላከያ ኢንዱስትሪ የዳበረ ልምድ ያላት አገር ናት።ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ተጠቃሚ ለማድረግ ምን የታሰበ ነገር አለ ?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** እስራኤል በሚያዚያ ወር 75ኛ የነጻነት በዓሏን ታከብራለች።በዚህ እድሜ ውስጥ እስራኤል በቴክኖሎጂ ከፍተኛ ደረጃ ደርሳለች።ከሰለጠኑት አገራት የማትተናነስ እንደውም በልጣ የምትገኝ አገር ናት።አውሮፓና አሜሪካ የእስራኤልን ቴክኖሎጂ ይፈልጋሉ።

በግብርናው፣ በትምህርቱ፣ በኢኖቬሽን በኩል በጣም የረቀቀች አገር ናት።በጸጥታው ዘርፍም ሰለጠንን ያሉ የዓለም አገራት ያልደረሱበትን ቴክኖሎጂ እየሰራች ትገኛለች።በቴክኖሎጂ ጉዳይ በኤዥያና ከትላልቅ አገራት ጋር በጋራ ትሰራለች፡፡

ሙቀትን በመሰብሰብ ኃይል በማመንጨት ሶላር ኢነርጂ (የጸሐይ ኃይል) ቴክኖሎጂን ያመጣችው እስራኤል ናት።በእስራኤል አገር የጸሀይን ብርሃን ወስዶ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ትልቅ ስራ እየተሰራ ነው።

በእስራኤል ከፍተኛ የውሀ እጥረት ስላለ የጨው ውሃን ወደ ንጹህ ውሃነት በመለወጥ ከእስራኤል አልፎ ለዮርዳኖስና ለፍልስጥኤም ሁሉ ይተላለፋል።በሀይቴክ የረቀቀ ጂፒኤስ ከእስራኤል የመጣ ቴክኖሎጂ ነው።

ከየትም የሚወነጨፍን ሚሳኤልን በሰማይ የሚያወድም የጨረር ቴክኖሎጂ አላት፤ ይህም በዓለም በአንደኛ ደረጃነት ላይ እንድትገኝ አድርጓታል።አሁን በስፋት ተስፋፍቶ የሚገኘው የድሮን ቴክኖሎጂም የተጀመረው በእስራኤል ነው።በግብርና፣ በቴክኖሎጂ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ዝናብን በማዝነብ ረገድ የበለጸገች አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ ለበርካታ ሺ ዘመናት ነጻነትዋን አስጠብቃ የኖረች አገር ናት፤ በዚህም በውጪ ኃይል ያልተደፈረች አገር መሆን ችላለች። ይህ የሚያሳየው ጠንካራና አንድነቱ ጠንካራ ህዝብ እንዳላት ነው።ከቴዎድሮስ ጊዜ ጀምሮ እስከ ንጉስ ኃይለሥላሴ ድረስ በርካታ ፈተናዎች ገጥመዋታል፤ ይሁን እንጂ ፈተናዎችን ሁሉ ማሸነፍ የቻለች ትልቅ አፍሪካዊት አገር ናት።

የፋሲል ቤተመንግስት፣ የላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያን፣ የጀጎል ግንብና አክሱምን የመሳሰሉ ቅርሶቿ ከፍ ያለ ስልጣኔ ባለቤት እንደነበረችም አመላካች ነው።በተፈጥሮ ሀብት የታደለች፤ ሰፊ የቆዳ ስፋት ያላት፣ ውሃ፣ ለም መሬትና በቂ ህዝብ ያላት ነች። ይህ ደግሞ በአጭር ጊዜ ወደ ስልጣኔ መምጣት የሚያስችላት አቅም ባለቤት እንደሆነች አመላካች ነው።በኤምባሲ ደረጃ የምንፈልገው ኢትዮጵያም ልክ እንደ እስራኤል በቴክኖሎጂ ጠንካራ እንድትሆን ነው።ሁሉቱም አገሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

በእስራኤል አገር ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት እንፈልጋለን።እስራኤል የቆዳ ስፋቷ ጠባብ ነው፤ ቴክኖሎጂን ተጠቅማ ከአሸዋ ላይ ከፍተኛ የሆነ ምርት ታመርታለች።ይህ ወደ ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ከፍተኛ ፍላጎት አላት።ምርምር በማድረግ በየወቅቱ የተለያዩ ሰብሎችን በመዝራት ከፍተኛ የሆነ ምርት ይገኛል።ወቅትን በመጠበቅ ሳይሆን ቴክኖሎጂን በመጠቀም በየጊዜው ምርት ማምረትን ይጠይቃል፡፡

የአቮካዶ ምርት ዝርያን ከእስራኤል በማምጣት በኢትዮጵያ እየተመረተ ነው።ከአራት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በማስረከብ በስፋት እየተመረተ ነው።ከአሜሪካ ጋር በጋራ የሚሰራ ፕሮጀክት ነው፤ በመላ አገሪቷ ለአርሶ አደሮች ተሰራጭቶ ከፍተኛ ምርት እየተገኘበት ነው።በትንሽ መሬት ላይ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ ነው።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት በኢትዮጵያ በጣም በሰፊው ለገበያ እየቀረበና እየተሸጠ ነው።ወደ ውጭም በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እየተገኘበት ይገኛል።የኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ ለአቮካዶ ምርት በጣም ተስማሚ ስለሆነ በስፋት እየተመረተ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እየሰራን ነው።ይህን በቴክኖሎጂ በመደገፍና አርሶ አደሩን በማላመድ ህዝቡ ከሚፈልገው በላይ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባል።ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ወደ ውጭ በመላክ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንድትሆን ሙከራ እየተደረገ ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ የሚሰማሩ ድርጅቶችም ከእስራኤል መጥተው እንዲሰሩ የተጀመሩ ስራዎች አሉ።በዚህም ለበርካታ ስራ አጥ ወጣቶች ስራ መፍጠር ይቻላል።እውቀቱን ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ጥቅም ላይ እንዲውል እየሰራን እንገኛለን።በቢሾፍቱ ከፍተኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በውሃ ላይ አትክልቶችን በማምረት ወደ ውጭ የመላክ ስራ እየተሰራ ነው።

እንዲህ አይነት ስራዎች በስፋት እንዲሰሩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፤ በመንግስት ትልቅ ትኩረት ከተሰጠው ለአገር ያለው ጥቅም ትልቅ ነው።አርሶ አደሮች እንዴት አድርገው አትክልትን በጓሮ ዘመናዊ በሆነ መልኩ እያመረቱ ከራሳቸው አልፈው ለገበያ ማቅረብ ይችላሉ በሚለው ዙሪያ ከ75 ሺ በላይ ለሚሆን አርሶ አደሮች በበጎ ፈቃድ ስልጠና ሰጥተዋል።ወደፊትም በስፋት ይሰራበታል፡፡

ከአፍሪካ አንደኛ የሆነው ካርጎ አልቆ ስራ ጀምሯል።ካርጎው ብዙ ሺ ቶን እቃዎችን እንዲያጓጉዝ ተደርጓል፤ ይህም በኢትዮጵያና በእስራኤል መካከል ያለውን የቴክኖሎጂ ልውውጥ ማሳያ ነው።ሁለተኛው እየተሰራ ነው።አዲስ አበባ ማዕከል ሆኖ በዛ ብዙ ሰዎች ሰልጥነው እንዲሰሩ የእስራኤል ኤሮስፔስና የኢትዮጵያ አየር መንገድ በጋራ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ሳይ በኢትዮጵያ የተደረሰበትን የሰላም ስምምነት እንዴት አገኙት?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** የሰላም ስምምነት መምጣቱ በጣም ጥሩና እስራኤልም የምትደግፈው ነው።ለአገር፣ ለሕዝብና ለመንግስት ሰላም በጣም ጠቃሚ ነው።በኢትዮጵያም የነበረው የወንድማማች ጦርነት ቆሞ ሰላም መምጣቱ ጥሩ ነው፤ እስራኤልም የምትፈልገውና የምትደግፈው ተግባር ነው።

ሰላም ሲኖር ብዙ ነገሮችን ሰርቶ መለወጥ ይቻላል።ሰላም ከሌለ ማንም አገር መጥቶ ማልማት አይችልም።የመጣውን ሰላም ተከትሎ የውጭ ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር ኢኮኖሚው እንዲረጋጋ ያደርጋሉ።

የስራ እድሎች እየበዙ በመጡ ቁጥር መረጋጋት ይሰፍናል፤ መንግስት ደግሞ ጥሩ አድርጎ መምራት እንዲችል ያደርገዋል።ለዲፕሎማሲያዊ ስራዎችም አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።እስራኤል ሰላሙ እንዲቀጥልና ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት በርካታ ስምምነቶች ተደርሰዋል። እነዚህ ወደ ተግባር እንዲቀየሩ እየተሰራ ነው።ሰላም መምጣቱን ተከትሎ ብዙ ስምምነቶች ይደርሳሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-በሁለቱ አገራት መካከል በልማት ዘርፍ የተጀመረውን ግንኙነት ለማጠናከር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ መንግስትና የህዝቡ ትኩረት ከልማት ይልቅ ጦርነቱን ማርገብ ነበር።ይህን ከባድ ፈተና አልፎ ወደ ልማቱ እየተገባ ነው።አሁን ጥሩ ጅማሮ አለ፤ በተለይ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት በጣም የሚደነቅ ነው።በእስራኤል ወቅት ተጠብቆ ሳይሆን ሁልጊዜም መስራት የተለመደ ነው፤ መሬት ጾም አያድርም።መሬት ያለ እረፍት ለህዝቦች ምርት መስጠት አለበት።

የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፤ እስራኤልም የሚያስፈልገውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ናት።ኢኮኖሚውም የሚያድገው መሬት ጾም እንዳያድር በማድረግ ነው።በእስራኤል አገር ከፍተኛ ሀብት የሚያንቀሳቅሱት የተለያዩ የግል ድርጅቶች በመሆናቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ ብሎም በእውቀት እንዲደግፉ ይደረጋል።

መንግስት አቅም ሲያንሰው፤ ግን ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ መንገዱን የማስተካከል ስራ ይሰራል፤ መንግስት አቅጣጫ ይሰጣል።በኢትዮጵያም መጥተው የስራ እድል እንዲፈጥሩ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።በዚህ ዘርፍ ትልቅ አቅም ያላቸው ድርጅቶች በእስራኤል አሉ፤ በኢትዮጵያም መጥተው መስራት ይፈልጋሉ፤ ለዚህ የሚሆን ጠንካራ የማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አለ።

በተለያዩ አገራት ያሉ ካምፓኒዎች ተስበው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ያለውን የአሰራር ሂደት በማቅለል የተፋጠነና ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል።በኢትዮጵያ የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ ይገባል።ለካምፓኒዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ካምፓኒዎች መጥተው ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል ይፈጥራሉ፤ ነገር ግን የዶላር እጥረት አለ በሚል ሽጠው ትርፉን መውሰድ አትችሉም እየተባሉ ነው።ከሚመጡበት አገር ከባንክ ይበደራሉ፤ በዚህ ሁኔታ ደግሞ መክፈል እየተቸገሩ ነው።ካልከፈሉ ደግሞ ባንኮች ገንዘባቸውን እንዳያንቀሳቅሱ ያደርጓቸዋል፤ ይህን መንግስት ማስተካከል አለበት፤ ካልሆነ ድርጅቶች አይመጡም።

ዋናው ማነቆና የስራ የእድል መፍጠር የማይቻለው በዚህ የተነሳ ነው።እስራኤልና ኢትዮጵያ በብዙ ነገር ሊጠቃቀሙ የሚችሉ አገሮች ናቸው።በተለያዩ የስራ ዘርፎች አብሮ መስራት የሚያስችል ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አዳብረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ፡፡**

**አምባሳደር አለልኝ፡-** እኔም ከአንጋፋው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ለነበረኝ ቆይታ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



ወርልድ ባንክን እንዲያስተዳድሩ የታጩት የማስተርካርድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የነበሩት አጄይ ባንጋ

## የቀድሞ ማስተርካርድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዓለም ባንክን እንዲመሩ ታጩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቀድሞ ማስተርካርድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዓለም ባንክን እንዲመሩ በአሜሪካ መታጨታቸው ተሰማ።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የቀድሞ ማስተርካርድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የነበሩት አጄይ ባንጋ የዓለም ባንክን እንዲመሩ በእጩነት አቅርበዋል።

አጄይ ባንጋ የሥልጣን ዘመናቸው ከመጠናቀቁ አንድ ዓመት ቀደም ብለው ሥራቸውን የሚለቁትን ዴቪድ ሚልፓስን እንደሚተኩ አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

እንደ አሶሼትድ ፕሬስ ዘገባ ዴቪድ ሚልፓስ ነዳጅን ለማግኘት ቅሪተ አካልን ማቃጠል የከባቢ አየርን ሙቀት ይጨምራል የሚለውን ሳይንስ በጥርጣሬ በመመልከት በመጠየቃቸው ምክንያት የሥራ ዘመናቸው አንድ ዓመት እየቀረው እንደሚለቁ ታውቋል።

በአሁኑ ወቅት አጄይ ባንጋ በአንድ የግል መዋዕለ ንዋይ አስተዳዳሪ ኩባንያ ከፍተኛ ኃላፊ ሲሆኑ፣ ከዚህ ቀደም ደግሞ ማስተርካርድ የተሰኘው አበዳሪ ኩባንያ ኃላፊ እንደነበሩ አሶሼትድ ፕሬስ አስታውቋል።

ባንጋ "የግልና የመንግሥት ሃብቶችን በማንቀሳቀስ የአየር ንብረት ለውጥን ጨምሮ ወቅታዊ የዓለማችንን ችግሮች ለመፍታት ተፈላጊው ልምድ አላቸው" ሲሉ ጆ ባይደን ተናግረዋል።

የአሜሪካ የግምጃ ቤት ኃላፊ ያኔት የለን ባወጡት መግለጫ ደግሞ፣ የባንጋ ልምድ የዓለም ባንክ ግቦች የሆኑትንና "አስከፊ ድህነትን ማጥፋትንና ብልጽግናን ማዳረስ" የሚሉትን ከዳር ለማድረስ ያግዛቸዋል ብለዋል።

በዓለማችን እንደልማድ ሆኖ አሜሪካ የዓለም ባንክ ኃላፊን ታጫለች። ባንጋ ቦታውን የሚያገኙ ከሆነ፣ በሕንድ የተወለዱ የመጀመሪያው የባንኩ መሪ ይሆናሉ ሲል ከሀገረ ሕንድ እስካሁን ድረስ ባንኩን የመራ እንደሌለ አሶሼትድ ፕሬስ አመላክቷል።

## የኒፕሲ ሀስል ገዳይ የ60 ዓመት እስራት ቅጣት ተፈረደበት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እ.አ.አ በ2019 ዓመተ ምሕረት ትውልደ ኤርትራዊውን የራፕ ሙዚቃ ኮከብ በመድረክ ስሙ ኒፕሲ ሀስል ወይም ኤርሚያስ አስገዶምን ሎስ አንጀለስ ከተማ መንገድ ዳር በጥይት የገደለው ሰው ትናንት ረቡዕ የ60 ዓመት እስራት ቅጣት ተፈረደበት።

ኤሪክ ኤ ሆልደር ሎስ አንጀለስ በሚገኘው በራፐሩ የልብስ መደብር ደጃፍ ላይ በፈጸመበት ግድያ እና ወንጀሉንም የፈጸመው በጥይት በመሆኑ በሃምሳ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የሎስ አንጀለስ ወረዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ኤች ክሌይ ጃክ ፈርደውበታል።

ግለሰቡ ኒፕሲ ሀስልን ተኩሶ በገደለበት ወቅት በአቅራቢያው የነበሩ ሌሎች ሁለት ሰዎች በጥይት በማቁሰሉ ደግሞ በተጨማሪ የ10 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ዳኛው ውሳኔ ሰጥተዋል።

በአንድ ወቅት የአንድ የወሮበላ ቡድን ተቀላቅሎ እንደነበረ የሚነገረው የራፕ ሙዚቃ ዘፋኙ ኒፕሲ ሀስል የተገደለው በሠላሳ ሦስት ዓመቱ ነው። በራሱ የልብስ መደብር ፊት ለፊት የተፈጸመበት ግድያ ያደገበትን የሎስ አንጀለስ አካባቢ ማኅበረሰብ እና ታላቅ ዝና ያተረፈበትን ሙዚቃ ሙያውን ባልደረቦቹን እና እንዲሁም የመጣበትን ማኅበረሰብ በሚጠቅሙ ሥራዎቹ የሚያደንቁትን እጅግ እንዳሳዘነ የሚታወስ ነው ።

ኒፕሲ ሀስል ከሕልፈቱ በኋላ እ አ አ በ2020 ዓመተ ምሕረት "ራክስ ኢን ዘ ሚድል" እና "ሀየር" በሚባሉት የራፕ ስልቶቹ የግራሚ ሽልማት ተበርክቶለታል።



ራፐር ኒፕሲ ሀስል እ.አ.አ በመጋቢት 29፣ 2018 በኦክላንድ፣ ካሊፎርኒያ ውስጥ የቅርጫት ኳስ ግጥሚያ ሲመለከት

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# የተማሪዎች ምደባ እና የመቁረጫ ነጥብ

**በለጥሻቸው ልዑልሰገድ**

በተለያየ ጊዜ ተማሪዎችም ሆኑ የተማሪ ቤተሰቦች የዩኒቨርሲቲ ምደባ እና የተማሪዎች ውጤት ላይ ቅሬታ ሲያሰሙ ይደመጣል። ከዚሁ በመነሳት ትምህርት ሚኒስቴር በጉዳዩ ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቷል። በማብራሪያው እጅግ ወሳኝ የሆኑ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን የተወሰኑትን በዚህ መልኩ አዘጋጅተን አቅርበናል።

ዩኒቨርሲቲዎች በየዓመቱ ያላቸውን የመቀበል አቅም ለትምህርት ሚኒስቴር እንደሚያሳውቁ የሚገልፀው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፤ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ምርጫቸውን በትምህርት ቤት በተወከለው መምህር አማካኝነት እንዲያሳውቁ ይደረጋል። ተማሪዎች ምርጫቸውን ሲሞሉ ሁለት ነገር ያካተተ ይሆናል፤ መማር የሚፈልጉትን የትምህርት ዘርፍና ሊማሩበት የሚፈልጉትን የትምህርት ተቋም። ይህንን ስራ የሚሰራው ፈተናው ተሰጥቶ ውጤት እስኪወጣ ባለው ጊዜ የነበረ ሲሆን ከሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ጀምሮ ተማሪዎች ምርጫቸውን እንዲሞሉ የሚደረገው ውጤት ከተገለፀ በኋላ ነው።

የተማሪዎችን ምርጫ ሲከናወን እንደተግዳሮት የሚገጥሙ ችግሮች አሉ፤ አንዳንዴ ከግንዛቤ እጥረት ተማሪዎች የመረጡበት የምርጫ ወረቀት ላይ የሚቀመጠውና መምህራን ወደ ሲስተሙ የሚያስገቡት የተለያየ ሊሆን ይችላል። ይህ ችግር በተደጋጋሚ ያጋጥም ነበር። ቢሆንም በሂደት እንዲስተካከል ተደርጓል። በቀጣይ ክፍተቶች ተለይተው በመስተካከላቸው ይህ ችግር ይገጥማል የሚል ስጋት እንደሌለ በመግለጫው ተጠቅሷል።

እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ገለፃ፤ ማንኛውም ተማሪ በመንግስትም ሆነ በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብቶ ለመማር ሀምሳ በመቶና ከዚያ በላይ ማምጣት ይጠበቅበታል። ይህም ማለት በተፈጥሮ ሳይንስ ከሚፈተኑት ሰባት ትምህርቶች 350 እና ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት አለባቸው፤ በማህበራዊ ሳይንስ ከሚፈተኗቸው ስድስት ትምህርቶች 300 እና ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም አይነስውራን ከሚፈተኗቸው አምስት ትምህርቶች 250 እና ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት ይኖርባቸዋል። ይህ ውጤት የመጀመሪያ ዲግሪን ለመማር የሚያስችላቸው ውጤት ነው።

የዩኒቨርሲቲዎች የመቀበል አቅምና ያለፈው ተማሪ ቁጥር የማይመጣጠን በሚሆንበት ጊዜ የመቁረጫ ነጥብ ይወጣል። የመቁረጫ ነጥብ ማለት ከግማሽ በላይ ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመቀበል አቅም በላይ ሲሆን ካለፉት ውስጥ ወደ መንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው መማር የሚችሉ ተማሪዎች የመግቢያ ነጥብ ነው።

በዚህ ዓመት ግማሽና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር ውስን ስለሆነ ለዚህ ዓመት ብቻ የሚያገለግል የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራመ ተዘጋጅቷል። ከግማሽ በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ ለመካተት 30 በመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብ አለባቸው። ይህ ማለት ግን 30 በመቶ ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በሙሉ የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራሙን በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ይከታተላሉ ማለት አይደለም። እነዚህም የሚማሩበት የትምህርት ፕሮግራም (መደበኛ ተማሪዎች)፣ ታዳጊ ክልሎች፣ አርብቶ አደር ክልሎች እንዲሁም አይነ ስውራንና መስማት የተሳናቸው ናቸው። በዚሁ መሰረት የአቅም ማሻሻያውን የሚወስዱ ተማሪዎች የመቁረጫ ነጥብ ይለያያል ማለት ነው።

ይህ ፕሮግራም ሲቀረፅ እድሉን የሚጠቀሙትን ለመለየትና የመቁረጫ ነጥብ ለማውጣት አራት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ይገባሉ። የመጀመሪያው የዩኒቨርስቲዎች የመቀበል አቅም ሲሆን በዚህ ዓመት በአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲዎች የመቀበል አቅም 14 በመቶ ወይም 136 ሺህ 777 ተማሪዎችን ነው። የተማሪዎች ውጤትና ትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ቦታም ወሳኝ እንዲሁም የሚማሩበት የትምህርት ፕሮግራም ሌሎች ከግምት የሚገቡ ነጥቦች ናቸው።

የቦታ ምደባ ላይ ብዙ ጊዜ ቅሬታ ሲቀርብ ይሰማል የሚለው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፤ የተማሪዎች የትምህርት ቦታ ምደባ የተቋማቱ የመቀበል አቅም፣ የተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ምርጫ እንዲሁም ያስመዘገቡት ውጤት መሰረት በማድረግ የሚመደብበት ነው። ምደባው በሚካሄድበት ወቅት በዩኒቨርሲቲው ሁሉም ትምህርት ቤቶች ውክልና እንዲኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፤ ቢሆንም ግን ትልቁን ቦታ የሚሰጠው ለተማሪ ምርጫ ነው።

ምደባው ከመካሄዱ በፊት አወንታዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የሚጠይቁ ተማሪዎች አሉ። እነዚህም በተለያየ ምክንያት በምዝገባ ወቅት ያልተመዘገቡ ተመሳሳይ ፆታ መንትዮች፣ የመፈተኛ ካርዳቸውን ከወሰዱ በኋላ የተለያዩ የጤና እክሎች የገጠሟቸው ተማሪዎች፣ የሚያጠቡ ሴት ተማሪዎች፣ በምዝገባ ወቅት አይነ ስውር መሆናቸው ሳይገለፅ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች እና የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከምደባ በፊት ማመልከቻ እንዲያስገቡ በሲስተሙ ላይ ማመልከቻ ማስገቢያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

በተለያየ ምክንያት በቅድመ ምደባው ማመልከት ያልቻሉ ተማሪዎች እድሉን እንዲያገኙ ከምደባ በኋላም የማመልከቻ ማስገቢያው ለአራት ቀናት ክፍት እንዲሆን ይደረጋል። ቢሆንም ግን በርካታ ሃሰተኛ የህክምና ማስረጃዎች በማስረጃነት ይቀርባሉ፤ የማጣራት ስራ ተሰርቶ ውድቅ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

በዚህ ዓመት ብቻ ሁለት ሺህ 948 ተማሪዎች የተሰጣቸው ምደባ ላይ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ሁሉም ቅሬታዎች ታይተው 18 ቅሬታዎች አወንታዊ መልስ ተሰጥቷቸዋል። ከነዚህ ውስጥ አስራ ስድስቱ ተመሳሳይ ፆታ መንትዮች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የሚያጠቡ እናቶች ናቸው።

በዚህ ዓመት በተማሪዎች ተመራጭ የሆነውና ብዙ ተማሪ በአንደኝነት የመረጠው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የማለፊያ ነጥብ ካመጡ 34 ሺህ ተማሪዎች ውስጥ 14 ሺ ተማሪ የመጀመሪያ ምርጫው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል። ሁለተኛ ደረጃ ተመራጭ ዩኒቨርሲቲ የሆነው ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የመቀበል አቅም ግን ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብልጫውን ይዟል፤ ሰባት ሺህ 500 ተማሪ የመቀበል አቅም አለው በማለት ይገልፃል።

# ስፖርት




## የአቃቂ ስታዲየም ዓለም አቀፍ መስፈርትን እንዲያሟላ እየተሰራ ነው

ብርሃን ፈይሳ

በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በመገንባት ላይ የሚገኘው የአቃቂ ዞናል ስታዲየም ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲኖረው እየተሰራ ነው። ቢሮው በከተማዋ የሚታየውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እጥረት ለመቅረፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑንም አስታውቋል።

ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በተመለከተ በአገር አቀፍ ደረጃ በየደረጃው ችግር መኖሩ ይታወቃል። ይህንን ችግር ለመፍታት በተለያዩ ከተሞች እየተገነቡ ከሚገኙ ስታዲየሞች መካከል አንዱ የአቃቂ ዞናል ስታዲየም ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ባለቤትነት እየተገነባ የሚገኘው ይህ ስታዲየም ሲጀመር የዞናል ደረጃ የተሰጠው እንደነበር ይታወቃል። ይሁንና ዓለም አቀፍ ደረጃን ሊመጥኑ የሚችሉ ማስተካከያዎችን በማድረግ እንደ አገር ያለውን ችግር መቅረፍ እንዲችል ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ቢሮው አስታውቋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን፤ ተጨማሪ መስራት የሚገባቸውን በማሟላት የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ደረጃን እንዲመጥን የዲዛይን ማስተካከያ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ስታዲየሙ በአሁኑ ወቅት የጣራ ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን፤ 20ሺ የሚሆኑ ጥራታቸውን የጠበቁ ወንበሮች የሚገጠሙለትም ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያያዘም የቢሮው ኃላፊዎች ወንበሮቹን እየሰራ በሚገኘው ሚድሮክ እህት ኩባንያ አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ በመገኘት ስለ ስራው ምልከታ አድርገዋል። ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶችንም ያሟላ ዘመናዊና ዓለም አቀፍ ሜዳ እንዲሆን ዲዛይኑ በፍጥነት ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውልና ችግሩም እንዲፈታ እየተሰራ



የአቃቂ ስቴድየም ከዞናል ደረጃ ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ አድጎ እንዲገነባ ስራዎች ተጀምረዋል፣

ነው። ይህ ስታዲየም ከዚህ ቀደም ይጠናቀቃል በሚል ከተያዘለት ጊዜ ሊዘገይ የቻለውም ከኮንትራክተሮችና ሌሎች ችግሮች ጋር በተያያዘ ነበር፤ በዚህ ወቅት ግን ተስተካክሎ በስራ ላይ እንደሚገኝ ነው ኃላፊው ያስገነዘቡት።

ከተማ አስተዳደሩ እንደ አገርም ሆነ እንደ ከተማ በዜጎች በተደጋጋሚ የሚነሳውን የስፖርት ማዘውተሪያዎች ችግር ለመፍታት በልዩ ትኩረት እየሰራ መሆኑንም አሳውቋል። ቢሮው ከስፖርት ጋዜጠኞች ጋር በነበረው የውይይት መርሃ ግብር ላይ በተደጋጋሚ ከተነሱ ችግሮች መካከል አንዱ ከማዘውተሪያ ስፍራ ጋር የተያያዘ መሆኑን ተከትሎም እየተሰሩ ያሉትን ስራዎች አብራርተዋል። በዚህም በእድሳት ላይ ቆይቶ አሁን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘውን የአበበ ቢቂላ ስታዲየም ቀሪ ስራዎችን በፍጥነት በማጠናቀቅ የኢትዮጵያ ቤትኪንግ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ እየተደረገ መሆኑንም የቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል። አማራጭ ስታዲየም እንደመሆኑ ሜዳው ላይ ያሉ ችግሮች እንዲስተካከሉ እየተደረገም ነው።

ችግሩ ከእግር ኳስ ባሻገር በሌሎች ስፖርቶችም የሚስተዋል እንደመሆኑ የራስ ኃይሉ የመዋኛ ገንዳ ጉዳይም ተነስቷል። ለረጅም ዓመታት በግንባታ ላይ የቆየው የመዋኛ ገንዳ በዚህ ወቅት በስራ ላይ ያለ ቢሆንም ቀሪ ስራዎች እንዲሁም የጥራት መጓደሎች አሉበት። ከዚህም ጋር ተያይዞ ማሽኖቹ የገቡት ከውጪ አገራት እንደመሆኑ ከባለሙያ ጋር የተያያዙ ቴክኒካዊ ችግሮች ገጥመዋል። በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

በየአካባቢው በብዛት አስፈላጊ የሆኑ የጥርጊያ ሜዳን እንዲሁም የ1ለ3 ሜዳዎችን በሚመለከትም በተለይ ትም ህርት ቤቶች ላይ በማተኮር እየተሰራ መሆኑንም ኃላፊው ጠቁመዋል። ከተማሪ ዎችና በየትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ ፕሮጀክቶች ባለፈ ከትምህርት ሰዓት ውጪ የአካባቢው ህብረተሰብም ተጠቃሚ መሆን በሚችልበት መልኩ ከትምህርት ቢሮ ጋር እየተሰራበት ነው። በየቦታው የሚገነቡ ሜዳዎችን በሚመለከትም በስፋት የሚስተ ዋለው ከአስተዳደር ጋር የተያያዘ ችግር ሲሆን፤ ይህንን ለመቅረፍ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ እስኪጸድቅ እየተጠበቀ ይገኛል።

በጥቅሉ በከተማዋ በትምህርት ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ላይ ወደ 900 የሚሆኑ ሜዳዎች መኖራቸው የታወቀ ሲሆን፤ ለተፈለጉበት ዓላማ እንዲውሉ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ኃላፊው አቶ በላይ አስታውቀዋል።


## Beeksisa caalbaasii ifaa lakk 02/2015

Godinaa Sh/Lixaatii Waajjiiri mallaqaa Aanaa Walmaraa bara baajata 2015 tiin Hojii seektarotaa Aanaaf kan oolu meeshaalee Barreessaa, Meeshaalee qulqullinaa, Meeshalee Elektroniksii, meeshaalee dhaabbataa biiroo keessaa, uffata seeraa hojjeetoota,Gommaa konkolaataafi motaraa Labsii bittaa mootummaa naannoo Oromiyaa Lakk.157/2002 fi Qajeelfama Bittaa mootummaa naannoo oromiyaa Lakk.02/2004 irratti hunda'udhaan caalbaasii ifaatiin dorgomsiisee bituu barbaada.

**Ibsa Balli'inaan**

Caalbasiin kun guyyaa Gaazexaa Addis Zaman irratti bahe calqabee gosota fi waliigala odeeffannoo meeshaalee bitamuuf barbadamanii kan ibsuu sanadaa caalbaasii qopha'ee qarshii hin deebine 300.00 (Dhibbaa Sadii) Abba Taayitaa Galiiwwan Aanaa Walmaraatte kaffaludhaan yeroo hundumaa sa'atti hojii waajjiraa Maallaqaa A/walmaraa Lakkofsaa 1 dhufudhaan bitachuun ni danda'ama.

**Dirqama Dorgoomtootaa /Ulaagaa Dorgomtootni guutuu qaban**

1. Gibiraa Bara kana kan kaffalanii fi facaatii dhiyeesii daldala meeshichaatiin heeyyama daldalaa haarome kan qaban, raga footokoppii isaa qabatamaa dhiyeessuu qabu.
2. Galma'aa taksii dabalata qabeenya kan ta'an fi footokoppii sartifiketii VAT dhiyeesuu qabu
3. Tarree dhiyesitootaa keessatti kan galma'anii fi raga galmee dhiyeessumaa ministeraa maallaqaa fi walta'insaa Dinaagdee dhiyeesuu kan danda'u.
4. Dorgomtootnii baay'ina gatii walii gala meeshaalee gosa bittaa dokumaantii tokko dorgomaan irraatti %1 kabachisaa caalbasii (CPO) dhaan kan qopha'ee qofa sanadaa caalbaasichaa waliin dhiyessuu qabu. Dorgomtootni maayikroo xixxiqaa (IMX) gosa bittaa fi baay'ina maallaqaa irratti dorgomanii ibsuudhaan qaama isaan gurmessee irraa waajjira Maallaqaa kallattiidhaan xalayaa wabummaa caalbaasii kanaaf dhiiyeessuu qabu.
5. Dorgoomtoni gatii meeshaalee tokko tokkoon ittiin dorgomaan sanadaa caalbaasii irratti qofa guutuudhaan orjinaalaa isaa fi koopii isaa adda addaatti (qofa qofaatti) Poostaa samsameen caalbasiin kun guyyaa gaazexaa irratti bahee eegaalee gaafa guyyaa 16ffaa Waaree booda hanga sa'attii 7:30 tti sanada caalbaasii saanduqa kanaaf qopha'ee keessaa galchuun kan dandeessan ta'ee sa'a kana irratii kan saamsamuu ta'a.
6. Dorgomaan kamiyyuu Meeshaalee naamunaa/saamudaa/ barbadaman Sanada gubaatii ibsamee yemmuu sanadaa guutee deebisuu waliin fidee galchuu qaba.
7. Caalbasiin kun guyyaa kana sa'attii 8:00tti dorgoomtotnii ykn bakka bu'onnii seraa isaanii fi qaamoleen irratti hirmaachuu barbaadan bakka argamanitti ni banamaa. Dhaabaatni caalbaasicha galchee ykn bakka bu'aan yoo jiraachuu baates poostaan isaanii ni banama.
8. Dorgoomtootni mo'aatan yeroo waliigaltee mallateessan gatii waligalaa meeshaalee mo'atanii % 10wabummaa raawwii caalbaasichaa baankiidhaan kan ragaasifamee (CPO) seraa qabessa ta'ee dhiyeessuu qabu. Dorgomtootni mo'ataman caalbaasichaa ergaa ifaa ta'ee booda kabachifnii caalbasiif galchaan fudhachuu ni danda'u
9. Dorgoomtotni caalbaasii kaną mo'aataan baasii kamiyyuu danda'uudhaan meeshaalee irratti mo'ataan guyyaa hojii 15(kudha shan) keessattii mana kuusaa waajjira maallaqaa fi walta'insaa Dinaagdee A/Walmaraattii dhiyyessuu qabu.
10. Waajjirichi mala ykn filannoo biraa yoo argatee caalbaasii kana gar tokkes ta'ee guuttumaan guutuutti haaqudhaaf mirga qaba.
11. Daldalaan kanaan duraa meeshaalee mo'atee waligaltee mallateessuu didee fi meeshaalee itti mo'atee hin dhiyyesinee dorgomuu hin danda'u.

**Odeeffannoo dabalataaf lakkoofsa bilbila 011-237-16-63/011-237-09-83**

**Teessoon Magaala Hoolataa Aanaa Walmaraa Finfinnee irraa gara Amboo km 28 irratti argama**

**Waajjiira Mallaqaa Aanaa Walmaraa**



## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1.ንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ SAKATA SEED CORPORATION.

አድራሻ፡ 2-7-1, Nakamachidai Tsuzuki-ku, Yokoham, Japan

2.የማልከቻ ቁጥር FTM/3116/2014 G.C

SAKATA

3.ምልክት፡

4.ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀም በ29/12/1999 ዓ.ም በVol-LXVI No. 359 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው::

5.የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ19/08/2021 እስከ 19/08/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል።

በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ባለሥልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-170 20/6/2015 (27/2/2023)



## ድሬዳዋ አስተዳደር

የባለንብረቱ ስም ሰኢድ ካሳ ሰኢድ ሰሌዳ ቁጥር 3-07178 ድሬ የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻንሲው ቁጥር JNITCS46120536458 የተሽከርካሪ ሞዴል TVTSLAF46INPRGAB.D ሞተር ቁጥር TD42-169805 የባለቤትነት ደብተር ጠፍቶብኛል ብለው በ 17/06/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሊብሬ /የባለቤትነት ደብተር/ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሉጀስቲክስ ባለሥልጣን**



## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ጀኒ ሉክማን የሱፍ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A14591 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር VF32AHFZE40658111 ሞዴል 206 የሞተር ቁጥር HFZ10FPS-3173826 የሊብሬ ቁጥር 158418/258788 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ8/6/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**